ወርእዪ፡ከመ፡ተጋብኡ፡ደቂቅኪ፡እምነበ፡
ምዕራበ፡ፀሐይ፡እስከነ፡ጽባሕ፡
ከፀሐይ ፡ መግቢያ ፡ ጀምሮ ፡ እስከ ፡
ፀሐይ ፡ መውጫ ፡ ድረስ ፡ ልጆችሽ ፡
እንደ፡ተሰበሰቡ፡እዩ፤

በቃሉ፡ለቅዱስ፡
በጌታ፡ቃል፤

ወይትፌሥሑ፡በዝክረ፡እግዚአብሔር፡
አምልኮተ ፡ እግዚአብሔርን ፡ በማ
ሰብ፡ደስ፡ይላችኋል፤

፮፤ወወጽኡ፡እምነቤኪ፡
ልጆችሽ፡ከአንቺ፡ተለይተው፡ወጡ፤

ወወሰድዎሙ፡ፀሮሙ፡በእግሮሙ፡
ጠላቶቻቸው ፡ በእግራቸው ፡ ማር
ከው፡ወሰዷቸው፤

ወያመጽኦሙ፡እግዚአብሔር፡ነቤኪ፡
እግዚአብሔር ፡ ወደ ፡ አንቺ ፡ ያመጣ
ቸዋል፤

እንዘ፡ይፀውርዎሙ፡በክብር፡ከመ፡መንበረ፡
ንጉሥ፡
እንደ፡ንጉሥ፡ዙፋን፡አንሣ፡አንሣ፡
እሽኮኮ፡እየተሸከሙ፡ያመጧቸዋል፤

፯፤ ወአዘዘ ፡ እግዚአብሔር ፡ ይትሐታ ፡
ኵሉ፡አድባር፡ነዋሐት፡
እግዚአብሔር ፡ ረጃጅሞች ፡ ተራ
ራዎች፡ይዋረዱ፡ዘንድ፡አዘዘ፡ማለት፡
ነገሥታቱ፡ይጠፉ፡ዘንድ፡አዘዘ፤

ወይምላዕ፡ኵሉ፡ማዕምቅ፡
ጐድጓዳው ፡ ምድር ፡ ሁሉ ፡ ይሞላ ፤

ወይዕሪ፡ምድር፡
ምድሩ፡ሁሉ፡የተካከለ፡ይሆን፡ዘንድ፤

ከመ ፡ ይሑር ፡ እስራኤል ፡ መጽያሕተ ፡
በስብሐተ፡እግዚአብሔር፡
እስራኤል ፡ እግዚአብሔር ፡ በሚያደ
ርገው ፡ በተአምራቱ ፡ (በጌትነቱ) ፡
ብትልም ፡ ጥርጊያውን ፡ ጐዳና ፡ ይዞ ፡
ይሔድ፡ዘንድ፤

፰፤ወይጼልሎሙ፡ኵሉ፡ዖም፡
ታላላቁ፡ዛፍ፡ሁሉ፡እስራኤልን፡ይጋ
ርዳቸዋል፤

ወኵሉ፡ዕፅ፡ሠናየ፡መዓዛ፡ለእስራኤል፡
በጎ፡መዓዛ፡ያለው፡ጥቃቅኑም፡ዛፍ፡
ሁሉ፡ይጋርዳቸዋል፤አንድም፡ወይጼ
ልሎሙ፡ኵሉ፡ዖም፡ጥቃቅኑ፡ዛፍ፡
ሁሉ፡ይጋርዳቸዋል፤ወኵሉ፡ዕፅ፡በጎ፡
ረድኤት፡ይደረግላቸዋል፤

በትእዛዘ ፡ እግዚአብሔር ፡ አምላከ ፡ እስ
ራኤል፤
በእስራኤል፡ፈጣሪ፡በእግዚአብሔር፡
ትዕዛዝ፤

በፍሥሓ፡
በተድላ፡በደስታ፤

ወበብርሃነ፡ስብሐቲሁ፡
በጌትነቱ፡ብርሃን፡ረድኤት፤

ወበምሕረቱ፡
በቸርነቱ፤

ወበጽድቁ፡
በይቅርታው [illegible]



## ሰቆቃወ ፡ ኤርምያስ ፤
## ምዕራፍ፡፩፤
## ጉባዔ፤

ወእምዝ፡እምድኅረ፡ዔወውዎ፡ለኤርምያስ፤
ኤርምያስን ፡ ከማረኩት ፡ በኋላ ፡
በቤሩት ፡ አፋፍ ፡ ቁሞ ፡ የተናገረው ፡
ልቅሶ ፡ ይህ ፡ ነው፤ አንድም ፡
በማረኩት፡ ጊዜ ፡ የተናገረው ፡ ልቅሶ ፤
አንድም ፡ እምቅድመ ፡ ይዔውውዎ ፡
ይላል፡ ሳይማርኩት ፡ ተከበው ፡ ሳሉ ፡
የተናገረው ፡ ልቅሶ ፤ አንድም ፡
ያለቀሰው፡ልቅሶ፡ይህ፡ነው፤

ወለኢየሩሳሌምኒ፡አማሰንዋ፡
ኢየሩሳሌምንም ፡ ሳያጠፏት ፤ አን
ድም ፡ ባጠፏት ፡ ጊዜ ፤ አንድም ፡
ካጠፏት ፡ በኋላ ፡ የተናገረው ፡ ልቅሶ ፡
ይህ፡ነው፤

ነበረ፡ኤርምያስኒ፡ይበኪ፡
ኤርምያስ፡ሲያለቅስ፡ኖረ፤

ወአስቆቀወ፡ዘከመዝ፡ሰቆቃወ፡ላዕለ፡ኢየሩ
ሳሌም፤
በኢየሩሳሌም ፡ ላይ ፡ እንደእዚህ ፡ ያለ ፡
ልቅሶን፡አለቀሰ፤

፩፤አሌፍ፤
አሐዱ ፡ እግዚአብሔር ፡ ማለት ፡ ነው፤
ይህን ፡ አሌፋት ፡ ለኄኖስ ፡ በጸፍጸፈ ፡
ሰማይ ፡ አሳይቶት ፡ ጽፎታል፤ ከዚህ ፡
አስቀድሞ ፡ የአቤል ፡ ደም ፡ ያጥፋን ፤
እያሉ፡ሲምሉ፡ነበር፤በዕሩቅ፡ብእሲ፡
ደም ፡ መማል ፡ አይገባም ፡ ብሎ ፡
ወውእቱ፡ዘአኀዘ፡ይጸውእ፡ስመ፡እግ
[illegible]
ምክንያቱ [illegible]

አምሳል ፡ ኋላም ፡ ነቢያት ፡ ግናያት ፡
አድርሰው ፡ ያሥሩበት ፡ ነበር ፤ ዛሬ ፡
እኛ፡ በአቡነ ፡ ዘበሰማያት ፡ ጸሎታ
ችንን ፡ እንድናሥር፤ ዳዊትም ፡
አግብቶ፡ ተናግሮታል፤ ኤርምያስ ፡
አራት፡ጊዜ፡መላልሶ፡ተናግሮታል፤

እፎ ፡ ነበረት ፡ ባሕቲታ ፡ ሀገር ፡ እንተ ፡
ምልዕት፡ሕዝበ፡
ሰው ፡ መልቶባት ፡ ትኖር ፡ የነበረች ፡
ሀገር፡እንደምን፡ብቻዋን፡ቀረች፤

ወኮነት፡መበለተ፡
ከሰው፡ከእንስሳ፡ተለይታ፡እንደምን፡
ድኃ፡ሆነች፤አንድም፡አንድ፡እግዚአ
ብሔርን ፡ አላመልክ ፡ ብላ ፡ ብዙ ፡
ጣዖታትን፡አምልካ፡እንደምን፡ድኃ፡
ሆነች፤

እንተ፡ትኴንን፡አሕዛበ፡
ብዙ፡አሕዛብን፡ትገዛ፡የነበረች፤

ወትኴንን፡በሐውርተ፡
ሀገሩን፡ሁሉ፡ትገዛ፡የነበረች፤

ወገብአት፡ውስተ፡እደ፡ጸዋር፡
በጠላቷ ፡ እጅ ፡ እንዴት ፡ ወደቀች ፤
እንዴት፡ተያዘች፡ብትልም፤አንድም፡
እግዚአ ፡ ኵሉ ፡ ጌታን ፡ አላመልክ ፡
ብላ፡ ኅሡር ፡ ጣዖትን ፡ አምልካ ፡
በጣዖት ፡ እጅ ፡ እንዴት ፡ ወደቀች ፤
አንድም ፡ ውስተ ፡ እደ ፡ ጸዋር፡ ቢል ፡
ግብር ፡ ይሸከሙላታል ፤ አንድም ፡
ግብር ፡ ይሸከሙላት ፡ በነበሩ፡ ሰዎች ፡
እጅ፡ላይ፡እንዴት፡ወደቀች፤

፪፤ቤት፤
ባዕል ፡ ማለት ፡ ነው ፡ ቢያገናኙት ፡ አ፡
[illegible] ማለት ፡ ነው ፤ የሚገናኝ ፡ የመጀ
መሪያው ፡ የመጨረሻው ፡ ነው ፡

www.ethiopianorthodox.org

ብካየ፡በከየት፡በሌሊት፡

በሌሊተ ፡ መከራ ፡ ተይዛ ፡ ሳለች ፡ ልቅሶን ፡ አለቀሰች ፤ አንድም ፡ ባዕል ፡ እግዚአብሔርን ፡ አላመልክ ፡ ብላ ፡ ኀሡር ፡ ጣዖትን ፡ አምልካ ፡ ልቅሶን ፡ አለቀሰች ፤

ወአንብዓ፡ውስተ፡መልታሕታ፡ውኅዘ፡

ዕንባዋ፡በፊቷ፡ፈሰሰ ፤

ወኃጥአት ፡ ዘይናዝዛ ፡ እምኵሎሙ ፡ እለ ፡ ያፈቅርዋ፡

ከሚወድዷት ፡ ሰዎች ፡ ሁሉ ፡ የሚያረጋጋት፡አጣች ፤

ወተዓረርዋ፡ኵሎሙ፡ፍቁራኒሃ፡

ወዳጆችዋ፡ሁሉ፡ተጣልዋት ፤

ወኮኑ፡ላቲ፡ጸላዕተ፡

ለእርሷ፡ጠላት፡ሆኗት ፤ አንድም፡ባቲ፡ቢል፡ጠላት፡ሆኑባት ፤

፫፤ ጋሜል፤

ግሩም፡እግዚአብሔር፡ማለት፡ነው ፤

ፈለሰት፡ይሁዳ፡በኀሣራ፡

ይሁዳ ፡ በኃጢአትዋ ፡ ተማርካ ፡ ሔደች ፤ አንድም ፡ ግሩም ፡ እግዚአብሔርን ፡ አላመልክ ፡ ብላ ፡ ኀሡር ፡ ጣዖትን ፡ አምልካ ፡ በኃጢአትዋ ፡ ተማርካ፡ሔደች ፤

ወበዝኀ፡ቅኔሃ፡

የምትገዛው፡ሰባ፡ዘመን፡ነው ፤

ወነበረት፡ውስተ፡አሕዛብ፡

ተማርካ ፡ ሒዳ ፡ በአሕዛብ ፡ ሀገር ፡ ኖረች ፤

ወአልባ፡ዕረፍት፡

ዕረፍት፡የላትም ፤

ኵሎሙ ፡ እለ ፡ ዴገንዋ ፡ አኃዝዋ ፡ በማዕከል ፡ [illegible]

የተከተልዋት ፡ ሰዎች ፡ ሁሉ ፡ በአጐሰቈላት፡ሰዎች፡መካከል፡ያዟት ፤

፬፤ ዳሌጥ፤

ድልው፡እግዚአብሔር፡ማለት፡ነው፤ በተገናኝ፡ጋዳ፡ማለት፡ነው ፤

ፍናዊሃ፡ለጽዮን፡ይላህዋ፡

የጽዮን ፡ ጐዳናዎች ፡ ያለቅሳሉ ፤ የጐዳና፡ ማልቀሱ ፡ መጥፋቱ ፡ ነው ፤ ቀድሞ ፡ ለመሥዋዕት ፡ ሲወጡ ፡ ሲወርዱ ፡ ቀንቶ ፡ ነበርና ፤ አንድም፡ የጽዮን፡መንደሮች፡ያለቅሳሉ፤በመንደሮች፡ሰዎችን፡መናገር፡ነው ፤ ከዚህ፡ አስቀድሞ ፡ ፍሪዳውን ፤ ሙክቱን ፡ እየሠዉ፡በልተው፡ጠጥተው፡ተድላ፡ ደስታ ፡ ያደርጉ ፡ ነበርና ፡ ይህ ፡ ቀርቶባቸው ፤

እስመ፡አልቦ፡ዘይመጽእ፡ለበዓል፡

ለበዓል፡የሚመጣ፡የለምና ፤

ወማሰነ፡ኵሉ፡አናቅጺሃ፡

በሮችዋ ፡ ሁሉ ፡ ጠፍተዋልና ፤ አንድም፡ ኃያላኖችዋ ፡ ጠፍተዋልና፡ ያለቅሳሉ ፤

ወካህናቲሃኒ፡ይበክዩ፡

ካህናቱም፡ያለቅሳሉ ፤

ወደናግሊሃኒ፡ተዴወዋ፡

ቆነጃጅቱም፡ተማረኩ ፤

ወለሊሃኒ፡መሪረ፡ኮነት፡

ኀዘንተ ፡ ኮነት ፡ ሲል ፡ ነው ፤ እርሷም፡ ያዘነች ፡ ሆነች ፤ አንድም ፡ ኀሥርተ፡ ኮነት፡የጎሰቈለች፡ሆነች ፤

፭፤ ሄ፤

ህልው፡እግዚአብሔር፡ማለት፡ነው ፤

ወኮኑ፡እለ፡[illegible]

በእርሷ፡[illegible]



ጠላቶቿ ፡ መከራዋን ፡ አይተው ፡ ደስ ፡ አላቸው ፤

ወጸላእቲሃኒ፡ተፈሥሑ፡

ጠላቶቿ፡ደስ፡አላቸው፡

እስመ ፡ እግዚአብሔር ፡ አኅሠራ ፡ በብዝኀ ፡ ኃጢአታ፡

በኃጢአቷ ፡ ብዛት ፡ እግዚአብሔር ፡ አጐስቍሏታልና፡አዋርዷታልና ፤

ለሕፃናቲሃ ፡ ዬወውዎሙ ፡ በቅድመ ፡ እለ ፡ ማቀይዋ፡

ሕፃናቷንም ፡ መከራ ፡ ባጸኑባት ፡ ሰዎች፡ ፊት ፡ ማርከው ፡ ወስደዋቸዋልና፡ደስ፡አላቸው ፤

፮፡ ዋው፡

ዋህድ ፡ እግዚአብሔር ፡ ማለት ፡ ነው ፡ ቢያገናኙ ፡ ሃው ፡ ማለት ፡ ነው፡ ሃው ፡ እሳት ፡ እንዲል ፡ ትግሬ ፡ በብዝኃ ፡ ትንታጉ ፡ ለእሳት ፡ ባለው ፡ በብዝኃ ፡ ትንታጉ፡ለሃው፡እንዳለበት ፤

ሰለብዋ፡ለወለተ፡ጽዮን፡ኵሎ፡ትርሲታ፡

የጽዮንን ፡ ልጅ ፡ ሽልማቷን ፡ ሁሉ ፡ ማርከው፡ወሰዱባት ፤

ወኮኑ፡መላእክቲሃ፡ከመ፡አብሐኵ፡እለ፡ ተነጥኡ፡ዘይትረዓዩ፡

አለቆቿ ፡ ከመሠምሪያቸው ፡ እንደታጡ ፡ እንደ ፡ በጎች ፡ አውራዎች ፡ ሆኑ፡ ማለት ፡ እነዚያ ፡ እንዲባክኑ ፡ እንዲከሱ፡ጠፉ ፤

ወሖሩ ፡ ድኩማኒሆሙ ፡ በቅድመ ፡ እለ ፡ ሮድዎሙ ፤

በከበቡዋቸው ፡ ሰዎች ፡ ፊት ፡ ደክመው፡ኖሩ ፤

፯፡ ዛይ፡

ዘከር፡እግዚአብሔር፡ማለት፡ነው፡

ተዘከረት፡ኢየሩሳሌም፡መዋዕለ፡ኃሣራ፡

ኢየሩሳሌም ፡ የመከራዋን ፡ ወራት ፡ አሰበች ፤

በኵሉ፡ፍትወታ፡ዘቀዲሙ፡

አስቀድማ ፡ ወድዳ ፡ በሠራችው ፡ ኃጢአቷ፡ሁሉ፡የመከራዋን፡ወራት፡ አሰበች ፤

ሶበ፡ወድቀ፡ሕዝባ፡በእደ፡ፀሮሙ፡

ወገንዎቿ ፡ በጠላቶቻቸው ፡ እጅ ፡ በወደቁ፡ጊዜ ፤

ወአልቦ፡ዘይረድኣ፡

የሚረዳት፡የለም ፤

ወርእይዋ፡ጸላዕታ፡በኀበ፡ፈለሰት፡

ጠላቶችዋ ፡ በተማረከችበት ፡ ቦታ ፡ አይዋት ፤

ወሰሐቅዋ፡

ዘበቱባት ፤

፰፤ ሔት፡

ሕያው ፡ ሕይወት ፡ እግዚአብሔር ፡ ማለት፡ነው፡ቢገናኝ፡ዛሕን፡ወመርስ፡ ማለት፡ነው ፤

አብሶ፡አበሰት፡ኢየሩሳሌም፡

ኢየሩሳሌም፡ፈጽማ፡በደለች ፤

ወበእንተ፡ዝንቱ፡ኮነት፡ሰቆራረ፡

ስለዚህ፡ነገር፡የምታጸይፍ፡ሆነች ፤

ኵሎሙ፡እለ፡ይዌድስዋ፡አኅሠርዋ፡

የሚያመሰግኑዋት ፡ ሰዎች ፡ ሁሉ ፡ አዋረድዋት፡አጐሠቈልዋት ፤

እስመ፡ርእዩ፡ኃሣራ፡በኀበ፡ተመንደበት፡

መከራ ፡ በተቀበለችበት ፡ ቦታ ፡ ተዋርዶዋን፡አይተዋልና ፤

ወወድቀት፡ድኅሪተ፡

ወደ፡ኋላ፡ወደቀች፡ማለት፡ወደ፡ኋላ፡

www.ethiopianorthodox.org

አ፡አብ፡ኵሉ፡ሰዓታት፡ጋዳ፡ለከ፡
አብ፡ሆይ፡በሰባቱ፡በአሥራ፡ሁለቱ፡
በሃያ፡አራቱ፡ጊዜያት፡የሚጸለየው፡
ጸሎት ፡ የሚቀርበው ፡ ምስጋና ፡
የአንተ፡ገንዘብ፡ነው፤እጅ፡መንሻህ፡
ነው ፡ ብትልም ፡ በዘር ፡ መካከል ፡
ይጽፈዋል፡ በንባብ ፡ መካከል ፡
ብትልም፤

በእንተ፡ዝንቱ፡እበኪ፡አነ፡
ስለዚህ፡ነገር፡እኔ፡አለቅሳለሁ፤

ዓይንየ፡አውኃዘ፡ማየ፡
ዓይኔ፡ዕንባን፡አፈሰሰ፤

እስመ፡ርኅቀ፡እምኔየ፡ዘይናዝዘኒ፡
የሚያረጋጋኝ፡ሰው፡ከእኔ፡ርቋልና፤

ወዘያገብእ፡ለነፍስየ፡
ሰውነቴን ፡ ከኃዘን ፡ የሚመልሳት ፡
የለምና፡ዓይኔ፡ዕንባን፡አፈሰሰ፤

ወማሰኑ፡ደቂቅየ፡
ልጆቼ፡ጠፉ፤

እስመ፡ሞዓ፡ፀር፡
ጠላት፡ድል፡ነሥቷልና፡ጠፉ፤

፲፯፡ ፌ፡
ፍቁር፡ማለት፡ነው፤አንድም፡ፍቅር፡
እግዚአብሔር፡ማለት፡ነው፤
እስመ ፡ እግዚአብሔር ፡ ፍቅር ፡ ውእቱ ፡
እንዲል፡

አንሥአት፡እደዊሃ፡ጽዮን፡
ጽዮን ፡ እስራኤል ፡ እጇን ፡ እያርገበ
ገበች ፡ ተማርካ ፡ ሔደች ፤ አንድም ፡
ቃሏን ፡ አሰምታ ፡ እያለቀሰች ፡
ተማርካ፡ሔደች፤

ውኅጥአት፡ዘይላህያ፡
ደስ ፡ የሚያሰኛት ፡ ወዳጅ ፡ ዘመድ ፡
አጣች፤

ይእግትዎ፡እለ፡ይረውድዎ፡
የሚከቡ፡ሰዎች፡ይከቡት፡ዘንድ፡እግ
ዚአብሔር፡በያዕቆብ፡አዘዘበት፤

ወኮነት፡ኢየሩሳሌም፡ትክተ፡በማዕከሎሙ፤
ኢየሩሳሌም ፡ በመካከላቸው ፡ ግዳጅ ፡
እንደያዛት ፡ ሴት ፡ ሆነች ፡ ማለት ፡
ግዳጅዋን ፡ ሲያዩባት ፡ ታፍራለችና ፡
መከራዋን ፡ መናገር ፡ ነው ፤ አንድም ፡
ድክምተ ፡ ሲል ፡ ነው ፤ በመከራ ፡
የደከመች፡ሆነች፤

፲፰፡ ጻዴ፡
ጻድቅ ፡ እግዚአብሔር ፡ ማለት ፡ ነው ፡
ቢያገናኙት፡ፋፃ፡ረቂቅ፡ማለት፡ነው፤
ከመ ፡ ፋፃ ፡ ቀጢን ፡ ወከመ ፡ መሰንቆ ፡
ሐዋዝ ፡ ያሥተፌስሕኒ ፡ ልብየ ፤
በሰሚያቱ፡እንዲል፤

ጻድቅ፡ውእቱ፡እግዚአብሔር፡
እግዚአብሔር፡ቸር፡እውነተኛ፡ነው፤

እስመ፡ወህክዎ፡ለአፉሁ፡
በቃሉ፡ተናግሮ፡፡የሠራውን፡ሕጉን፡
በማፍረስ፡አነሣስቼዋለሁና፤

ስምዑ፡ኵልክሙ፡አሕዛብ፡
አሕዛብ፡ሁላችሁም፡ስሙ፤

ወርእዩ፡ቍስልየ፡
ቍስለ፡መከራዬን፡ተመልከቱ፤

እስመ ፡ ዔወውዎሙ ፡ ለደናግልየ፡ ወለወራ
ዙትየ፡
ጐልማሶቼን ፡ ቆናጆቱን ፡ ማርከዋቸ
ዋልና፤

፲፱፡ ቆፍ፡
ቅሩብ፡እግዚአብሔር፡ማለት፡ነው፤

ጸዋዕክዎሙ፡ለመሐዛንየ፡ወተጸመሙኒ፡
ወዳጆቼን ፡ ...



ካህናትየ፡ወረበናትየ፡ሐልቁ፡
ካህናቱ፡መምህራኖቼ፡ጠፉ፤

በሀገር ፡ ሶበ ፡ ሐሠሡ ፡ ዘይበልዑ ፡በዘይ
መይጡ፡ነፍሶሙ፡ወኀጥዑ፤
ሰውነታቸውን፡በሚመልሱ፡ገንዘብ፡
በከተማ፡የሚበሉት፡(በሹ)፡በፈለጉ፡
ጊዜ፡አጡ፤

፳፡ ሬስ፡
ርዑስ ፡ ማለት ፡ ነው ፡ ቢያገናኙት ፡
ኳራ፡ፀሐይ፡ማለት፡ነው፤
አብ ፡ ኳራ ፡ ወልድ ፡ ኳራ ፡ መንፈስ ፡
ቅዱስ፡ኳራ፤እንዲል፡የአገው፡ቄስ፡
የቀ ፡ ጸያፍ ፡ አለበትና ፡ አብ ፡ ፀሐይ ፡
ወልድ ፡ ፀሐይ፡ መንፈስ ፡ ቅዱስ ፡
ፀሐይ፡ሲል፡ነው፤

ርኢ፡እግዚእ፡
አቤቱ፡መከራዬን፡እይ፡ተመልከት፤

እስመ፡ሐመምኩ፡
መከራ፡ተቀብየአለሁና፤

ወተከውሰ፡ከርሥየ፡
ሰውነቴ፡ተናዋውጧልና፤

ወልብየኒ፡ተመይጠ፡ላዕሌየ፡
ልቡናዬም፡ወደ፡ኃዘን፡ተመለሰ፤

እስመ፡መሪረ፡መረርኩ፡
ፈጽሜ፡በመከራ፡ተጨንቄያለሁና፤

በአፍአኒ፡እምኮነተኒ፡መጥባሕት፡
በዘመቻ፡ጦር፡የወላድ፡መካን፡አደረ
ገችኝ፤

ወብድብድ፡በውስተ፡ቤት፡
ቸነፈርም፡በቤት፡ልጆቼን፡አጠፋ፤

፳፩፡ ሳን፡
ስቡሕ፡እግዚአብሔር፡ማለት፡ነው፤
...

እንደሆነ፡ሳምኬትን፡ሰፋኒ፡ማለት፡
ነው፤

ስምዑኒ፡ዘከመ፡እግዕር፡አነ፡
እኔ፡በመከራው፡ተይገፎ፡እንድጮህ፡
ስሙኝ፤

ወአልቦ፡ዘያልህየኒ፡
ደስ ፡ የሚያሰኘኝ ፡ ወዳጅ ፡ ዘመድ ፡
የለምና፤

ኵሉ፡ፀርየ፡ሰምዑ፡ሕማምየ፡ወተፈሥሑ፡
ጠላቶቼ፡ሁሉ፡መከራዬን፡ሰምተው፡
ደስ፡አላቸው፤

እስመ ፡ አንተ ፡ ገበርከ ፡ ዘአምጻእከ ፡ ዕለተ ፡
ወጸዋዕከ፡
የመከራን ፡ ቀን ፡ ጠርተህ ፡ ያመጣህ ፡
አንተ፡ይህን፡አድርገሃልና፤

ወኮኑ፡ከማየ፡
አሕዛብ፡እንደ፡እኔ፡ሆኑ፡ማለት፡እኔ፡
እንድማርክ ፡ የሚማርኩ ፡ ሆኑ ፤
አንድም ፡ ይኩኑ ፡ ከማየ ፡ ቢል ፡ ዛሬ ፡
እኔ፡ እንደ ፡ ማረከሁ ፡ የሚማርኩ ፡
ይሁኑ፤

፳፪፡ ታው፡
ትጉህ ፡ እግዚአብሔር ፡ ማለት ፡ ነው ፡
ቢያገናኙት ፡ ስታው ፡ እግዝእት ፡
ማለት ፡ ነው ፤ ሰቲ ፡ መሪማ ፡ እንዲል ፡
ዓረብ፡እግዝእት፡ሲል፡ነው፤

ለትባእ፡ኵሉ፡እከዮሙ፡ቅድሜከ፡
ክፋታቸው፡ሁሉ፡በፊትህ፡ትድረስ፤

ወተቃረሞሙ ፡ ዘከመ ፡ ተቃረምከ ፡ ኪያየ፡
አንተ፡በኵሉ፡ኃጢአትየ፡
በፍጹም፡ኃጢአቴ፡አንተ፡እኔን፡በመ
ከራ፡እንደለቀምኸኝ፡ልቀማቸው፤

እስመ፡በዝኃ፡ናህክየ፡
ልቅሶ ፡ ኀዘኔ ፡ ናዕከየ ፡ ቢል ፡ ዕኑ ፡
መከራዬ፡በዝቷልና፤

www.ethiopianorthodox.org

ወልብየኒ፣ያጠውቀኒ፣
ልቡናዬ ፡ በመከራው ፡ ያስጨንቀኛል።

## ምዕራፍ ፡ ፪ ፣

፩፣ አሌፍ፣
አሐዱ፣እግዚአብሔር፣ማለት፣ነው፤

እፎኬ ፣ አደመና ፣ እግዚአብሔር ፡ በመቅሠፍተ፣መዓቱ፣ለወለተ፣ጽዮን፣
ቁጣውን ፣ በሚፈጽምበት ፡ መዓት ፡ መቅሠፍት ፡ እግዚአብሔር ፡ የጽዮንን ፡ ልጅ ፡ ቤተ ፡ እስራኤልን ፡ እንዴት፣አጠቈራት፤

ወነጽሐ ፣ እምሰማይ ፣ ውስተ ፡ ምድር ፣ ለክብረ፡እስራኤል፣
ክብርት ፣ እስራኤል ፡ ሲል ፡ ነው ፡ ክብርት ፣ የምትሆን ፣ እስራኤልን ፡ ከምድር ፡ አንሥተው ፡ የጣሉት ፡ እንዲኀዳ ፡ የሚኀዳ ፡ መከራ ፡ አመጣባት፤አንድም፣ከክብር፡አዋረዳት፤

ወተዘከረ፣መከየደ፣እገሪሁ፣በዕለተመዓቱ፡
ማደሪያው ፡ እስራኤልን ፡ በመዓት ፡ አሰበ ፣ ኢተዘከረ ፣ ቢል ፡ ማደሪያው ፡ እስራኤልን፡በምሕረት፣አላሰበም፣

፪፣ ቤት፣
ባዕል፡እግዚአብሔር፣ማለት፡ነው፤

አስጠመ፣እግዚአብሔር፣ወኢመሐከ፡ኵሎ፣መሠንዮ፣ለያዕቆብ፣
እግዚአብሔር፡እስራኤልን፡በባሕረ፡መከራ፡አሠጠመ፤

ወኢመሐከ፡ኵሎ፣መሠንዮ፣ለያዕቆብ፣
ለያዕቆብ ፣ ለአማረው ፣ ገንዘብ ፡ ሁሉ፡ አልራራለትም፤

ወአንኀለ ፣ በመዓቱ ፣ አጽዋኒሃ ፣ ለወለተ ፣ ይሁዳ፣
ተቆጥቶ ፡ በአመጣው ፡ በመዓቱ ፡ የይሁዳን ፡ ልጅ ፣ አምባዋን ፡ አፈረሰ፤ አንድም፡ኃያላንዋን፡አጠፋ፤

ወአጥበቃ፣በምድር፣
ከምድር፡አጣበቃት፡በስልት፡ያዛት፤

ከመ፡ኢትርአይ፣
ቀና፡ብላ፡እንዳታይ፡ ስልት፡የያዘው፡ ሰው፡ቀና፡ብሎ፡ማየት፡ይሳነዋልና፤ አንድም፡በባቢሎን፡አዘገያት፤

ወአርኰሰ፣መንግሥታ፣ወምኵናኒሃ፣
መንግሥቷን ፡ ጉልቷን ፡ አረከሰ ፡ አጐሰቆለ፤

፫፣ ጋሜል፣
ግሩም፡ማለት፡ነው፤

ቀጥቀጠ፡በመዓቱ፡ኵሎ፡ቀርነ፡እስራኤል፣
የእስራኤልን ፡ ሥልጣን ፡ በመዓቱ ፡ አጠፋ ፤ አንድም ፡ የእስራኤልን ፡ ንጉሥ፡አጠፋ፤

ወሜጠ፡ድኅረ፡የማኖ፡እምገጸ፡ፀር፣
ሥልጣኑን ፡ ከጠላቶቿ ፡ ፊት ፡ ወደ ፡ ኋላ፡መለሰ፡ማለት፡የማይረዳት፡ሆነ፤

ወአንደደ፡ላዕለ፡ያዕቆብ፡ነበልባለ፡እሳት፣
በያዕቆብ፡መከራን፡አመጣ፤

ወበልአ፡ኵሎ፡ዘዓውዱ፣
በዙሪያው፡ያለውን፡ሁሉ፡አጠፋ፤

፬፣ ዳሌጥ፣
ድልው፡ማለት፡ነው፤

ወሰቀ፡ቀስቶ፡ከመ፡ፀር፣
ወዳጅ፡የነበረ፡እግዚአብሔር፡እንደ፡ ጠላት፡ቀስቱን፡ሳበ፤

ወከመ፡ጸላኢ፡አጽንዐ፡የማኖ፣
እንደ፡ጠላት፡ሥልጣኑን፡አጸና፤



ወቀተለ፡ኵሎ፡ዘያፈትዋ፡ለዓይንየ፡
ለዓይኔ ፡ ደስ የሚያሰኘትን ፡ ሁሉ ፡ አጠፋ፤

ወላዕለ ፡ ተዓይኒሃ ፡ ለወለተ ፡ ጽዮን ፡ ከዓወ ፡ መዓቶ፡ከመ፡እሳት፡
በጽዮን፡ልጅ፡በሠራዊቶቿ፡መዓቱን፡ አብዝቶ፡አመጣ፤

፭፣ ሄ፡
ሕልው፡ማለት፡ነው፤

ኮነኒ፡እግዚአብሔር፡ከመ፡ፀር፡
ወዳጄ፡የነበረ፡እግዚአብሔር፡እንደ፡ ጠላት፡ሆነብኝ፤

ወአስጠሞ፡ለእስራኤል፡
እስራኤልን ፡ በባሕረ ፡ መከራ ፡ አሰጠመው፤

ወአስጠመ፡ኵሎ፡ክበዲሃ፡
ገንዘቧንም፡ሁሉ፡አጠፋ፤

ወአማሰነ፡አጽዋኒሃ፡
አምባዎቿን፤አፈረሰ፤አንድም፡ኃያላኖችዋን፡አጠፋ፤

ወአብዝኀ፡ኃዛራ፡ለወለተ፡ይሁዳ፡ኀሥርት፡
ጐስቋላ፡የምትሆን፡የይሁዳን፡ልጅ፡ ተዋርዶዋን፡አበዛ፤

፮፣ ዋው፡
ዋሕድ፡እግዚአብሔር፡ማለት፡ነው፤

ጸለለ፡ከመ፡ወይን፡ማኅደሮ፡
ወይን ፡ ያለበትን ፡ ቦታ ፡ እንዲሸፍን ፡ እስራኤልን ፡ በመከራ ፡ ሸፈናት ፤ አንድም ፡ ወጸለለ ፡ ማኅደሮ ፡ እግዚአብሔር ፡ ማደሪያው ፡ እስራኤልን ፡ በመከራ፡ሸፈነ፤

ከመ፤ወይን፣
ወይን፡ያለበትን፡ቦታ፡እንዲሸፍን፤

ወአማሰነ፡ኵሎ፡በዓሎ፡
በዓሉን፡ሁሉ፡አጠፋ፤

ረስዐ፡እግዚአብሔር፡ዘገብረ፡በጽዮን፡በዓለ፡ ወሰንበተ፡
እግዚአብሔር፡በጽየን፡ያደርገው፡የነበረውን፡በዓል፡ሰንበትን፡ዘነጋ፤

ወአሕለቀ፡በመቅሥፍተ፡መዓቱ፡ነገሥተ፡
ተቆጥቶ ፡ ባመጣው ፡ መቅሠፍት ፡ ነገሥታቱን፤

ወመላእክተ፡
አለቆችን፤

ወካህናተ፡
ካህናቱን፡አጠፋ፤

፯፣ ዛይ፣
ዝኩር፡እግዚአብሔር፡ማለት፡ነው፤

ኀደገ፡እግዚአብሔር፡ምሥዋዖ፡
እግዚአብሔር፡ምሥዋዓ፡ብርትን፡ ተወ ፤ አንድም ፡ ምሥዋዓ ፡ ቅዳሴው ፡ እስራኤልን፡በረድዔት፡ተወ፤

ወረስአ፡መቅደሶ፡
ማደሪያው ፡ እስራኤልን ፤ አንድም ፡ ቤተ፡መቅደስን፡ዘነጋ፤

ዐጸወ፡በእደ፡ፀር፡ዓርፍተ፡ኃይላ፡
የሠራዊቷ ፡ መሠወሪያ ፡ የሚሆን ፡ ቅጽርዋን ፡ አፈረሰ ፤ አንድም ፡ ሠራዊቷን ፡ የሚይዙ ፡ መኳንንቷን ። አንድም፡የሠራዊቷ፡ጽንዕ፡የሚሆኑ፡ ኀያላኗን፡አጠፋ፤

ቃለ ፡ ወሀቡ ፡ ውስተ ፡ ቤተ ፡ እግዚአብሔር ፡ ወየበቡ፡ከመ፡ዕለተ፡በዓል፡
ትሩፍ ፡ እስራኤል ፡ በበዓል ፡ ቀን ፡ ያመሰግኑ ፡ እንደ ፡ ነበረ ፡ አሕዛብ ፡ በቤተ ፡ መቅደስ ፡ አወኩባት ፡ ደነፉባት፡አገረሩባት፤

www.ethiopianorthodox.org

፰፡ ሔት፡

ሕያው ፡ ሕይወት ፡ እግዚአብሔር ፡ ማለት፡ነው፤

ሚጠ ፡ ከመ ፡ ያማስን ፡ እግዚአብሔር ፡ ዐርፍታ፡ለወለተ፡ጽዮን፡

እግዚአብሔር፡የጽዮንን፡ልጅ፡የኢየ ሩሳሌምን ፡ ቅጽርዋን ፤ አንድም ፡ መዓቱን፡መለሰ፤

ወሰሀባ፡በአምጣነ፡ኃይሉ፡

እንደ ፡ ኃይሉ ፡ መጠን ፡ መከራውን ፡ አመጣባት፤

ወኢመጠወ፡እዴሁ፡እምአስጥሞ፡

ሥልጣኑን፡ከመዓት፡ወደ፡ምሕረት፡ አልመለሰም፤

ወለሀወ፡ጥቅማ፡

ግንቧ፤

ወዐረፍታ፡

ቅጽርዋ ፡ አለቀሰ ፤ አንድም ፡ ጥቅማ ፡ ንጉሥዋ ፡ ወዐርፍታ ፡ ኃያላኖቿ ፡ አለቀሱ፤

ወደከሙ፡ኅቡረ፡

አንድ፡ሁነው፡ደከሙ፡ማለት፡ጠፉ፤

፱፡ ጤት፤

ጠቢብ፡እግዚአብሔር፡ማለት፡ነው፤

ተደፍኑ፡ውስተ፡ምድር፡ዴዴያቲሃ፡

ደጃፎቿ፡በምድር፡ተቀበሩ፤አንድም፡ ኃያላኖቿ፡ጠፉ፤

ተገድፈ፡ወተቀጥቀጠ፡መናሥግቲሃ፡

ቊልፏ ፡ ተሰበረ ፤ አንድም ፡ ሠራ ዊቶቿ፡ጠፉ፤

ንጉሣሂ፡ወመልአካሂ፡ውስተ፡አሕዛብ፡

ንጉሷም፡አለቃዋም፡በአሕዛብ፡እጅ፡ ተማረኩ ፤ ወደ ፡ አሕዛብ ፡ አገር ፡ ተማርከው፡ሔዱ፡ብትልም፡

አልባቲ፡ሕግ፡

ሕግ፡የላትም፡አልነበራትም፤

ወነቢያቲሃ፡ኢርእዩ፡ራእየ፡በኀበ፡እግዚአ ብሔር፡

ነቢያቶቿም፡ከእግዚአብሔር፡ዘንድ፡ ተገልጦላቸው፡ራእይ፡አላዩም፤

፲፡ ዮድ፡

የማነ፡እግዚአብሔር፡ማለት፡ነው፤

ነበሩ፡ውስተ፡ምድር፡ወአርመሙ፡ረበናቲሃ ፡ለወለተ፡ጽዮን፡

የጽዮን ፡ ልጅ ፡ መምህራኖቿ ፡ በምድር፡ዝም፡ብለው፡ተቀመጡ፤

ወወደዩ፡መሬተ፡ውስተ፡ርእሶሙ፡

በራሳቸው፡ላይ፡ትቢያ፡ነሰነሱ፡ተዋ ርዶዋቸውን፡መናገር፡ነው፤

ወቀነቱ፡ሠቀ፡

ምንጣፍ፡ታጠቁ፤

ወአውረድዎሙ ፡ ውስተ ፡ ምድር ፡ ለመሳ ፍንት፡ወለደናግል፡በኢየሩሳሌም፡

በኢየሩሳሌም፡የሚኖሩ፡መሳፍንቱን፡ ቈናጅቱን፡ከአልጋ፡ወደ፡ምድር፡አወ ረዷቸው፤

፲፩፡ ካፍ፡

ከሀሊ፡እግዚአብሔር፡ማለት፡ነው፤

ደከማ፡አዕይንትየ፡በአንብዕ፡

ዓይኖቼ ፡ በዕንባ ፡ ደከሙ ፤ እንባን ፡ በማፍሰስ፡ደከሙ፡ብትልም፤

ደንገፀ፡ልብየ፡

ልቡናዬ፡ደነገጠ፤

ወተክዕወ፡ውስተ፡ምድር፡ክብርየ፡በእንተ፡ ቅጥቃጤሃ፡ለወለተ፡ሕዝብየ፡

የወገኔ ፡ ልጅ ፡ በመከራ ፡ ስለ ፡ ተቀጠ ቀጠች ፡ ሐሞቴ ፡ በምድር ፡ ፈሰሰ ፤ አንድም፡አእምሮዬ፡ጠፋ፤



ሶበ፡ኀልቁ፡ሕፃናት፡

ሕፃናቱ፡በጠፉ፡ጊዜ፤

ወጠባዊት፡በማዕከለ፡ሀገር፡

እናቶቻቸውም ፡ በከተማ ፡ መካከል ፡ በጠፉ፡ጊዜ፡ሐሞቴ፡ፈሰሰ፤

፲፪፡ ላሜድ፡

ልዑል፡እግዚአብሔር፡ማለት፡ነው፤

ወይቤልዎን፡ለእማቲሆን፡

እናቶቻቸውን፡እንዲህ፡አሏቸው፤

አይቴ ፡ እክል ፡ ወወይን ፡ ሶበ ፡ ርኅቡ ፡ ከመ ፡ ቅቱላን ፡ ውስተ ፡ መርሕበ ፡ ሀገር ፡ ሶበ ፡ ወጽአት፡ነፍሶሙ፡በውስተ፡ሕፅነ፡እሞሙ፡

በእናቶቻቸው ፡ ጭን ፡ ሁነው ፡ ሰውነ ታቸው ፡ እለይ ፡ እለይ ፡ ባለች ፡ ጊዜ ፡ ሕፃናቱ ፡ በከተማ ፡ ተወግተው ፡ እንደ ሞቱ ፡ ሰዎች ፡ ወዴት ፡ እህል ፡ አግኝተን፡ በልተን ፤ ወዴት ፡ ወይን ፡ አግኝተን፡ጠጥተን፡አሏቸው፤

፲፫፡ ሜም፡

ምዑዝ፡እግዚአብሔር፡ማለት፡ነው፤

በምንት፡አስተማስለኪ፡

በምን፡እመስልሻለሁ፤

ወበምንት ፡ አስተዔርየኪ ፡ ወለተ ፡ ኢየሩ ሳሌም፡

የኢየሩሳሌም፡ልጅ፡ከማን፡ጋራ፡አስ ተካክልሻለሁ፤

መኑ፡ያድኅነኪ፡

ማን፡ያድንሻል፤

ወመኑ ፡ ዘያስተፌሥሐኪ ፡ ወለተ ፡ ጽዮን ፡ ድንግል፡

ድልድል ፡ ቅምጥል ፡ የምትሆኚ ፡ የጽዮን ፡ ልጅ ፡ ደስ ፡ የሚያሰኝሽ ፡ ማነው?

እስመ፡ዓብየ፡ከመ፡ባሕር፡ቅጥቃጤኪ፡

መከራሽ፡እንደ፡ባሕር፡በዝቷልና፤

መኑ፡ይፌውሰኪ፡

ከመከራ፡የሚያድንሽ፡ማነው፤

፲፬፡ ኖን፡

ኖላዊ፡ንጉሥ፡ማለት፡ነው፤

ነቢያትኪ፡ርእዩ፡ለኪ፡ከንቶ፡

ነቢያቶችሽ፡ከንቱ፡ትምህርትን፡አስ ተማሩሽ፤

ወኢከሠቱ፡ጌጋየኪ፡ከመ፡ይሚጡ፡ፄዋኪ፡

ምርኮሽን፡ይመልሱ፡ዘንድ፡እንድት ማረኪ፡አልነገሩሽም፤

ወርእዩ፡ለኪ፡ተረፈ፡ከንቶ፡

ከንቱ፡ጣዖትን፡አስተማሩሽ፤

፲፭፡ ሳምኬት፡

ሰፋኒ፡እግዚአብሔር፡ማለት፡ነው፤

ጠፍሑ ፡ እደዊሆሙ ፡ ላዕሌኪ ፡ ኵሎሙ ፡ ኀላፍያነ፡ፍኖት፡

አሕዛብ ፡ ሁሉ ፡ በአንቺ ፡ ላይ ፡ እጃቸውን፡አጨበጨቡ፤

ተፋፀዩ፡

አፏጩ ፡ ብንጣሬ ፡ ሰው ፡ ይሰማናል ፡ ብለው፤አንድም፡የአንክሮ፤

ወአንቀሁ ፡ ርእሶሙ ፡ ላዕለ ፡ ወለተ ፡ ኢየሩ ሳሌም፡

በኢየሩሳሌም፡ልጅ፡ላይ፡ራሳቸውን፡ ነቀነቁ፤

ወይቤሉ ፡ ዛቲኑ ፡ ሀገር ፡ አክሊሉ ፡ ወክብሩ ፡ ወፍሥሐሁ፡ለኵሉ፡ምድር፡

እንደ ፡ ጅሮ ፡ ታላቅ ፡ እንደ ፡ ዓይን ፡ ታናሽ ፡ የለም ፤ ለዓለሙ ፡ መመኪያ ፡ የምትሆን፡ሀገር፡ይህች፡ናት፡አሉ፤

፲፮፡ ዔ፡

ዓቢይ ፡ እግዚአብሔር ፡ ማለት ፡ ነው ፡ ቢያገናኙት፡ሰዓታት፡ማለት፡ነው፤

www.ethiopianorthodox.org

አብቀዉ ፡ አፉሆሙ ፡ ላዕሌኪ ፡ ኵሎሙ ፡ ፀርኪ፡
ጠላቶችሽ ፡ ሁሉ ፡ በአንቺ ፡ ላይ አፋቸውን፡ከፈቱ፤

ተፋፀዩ፡
አፏጩ፤

ወሐቀዩ፡ስነኒሆሙ፤
ጥርሳቸውን፡አፋጩ፡ትምህርተ፡ፀብ፡ነው፤

ወይቤሉ፡ውሕጥናሃ፤
እንደ ፡ ጥሀሎ ፡ ዋጥናት ፡ እንደ ፡ እንቀት፡ጠጣናት፡አሉ፤

ወባሕቱ፡ዛቲ፡ዕለት፡ዘተሰፈውናሃ፤
ነገር፡ግን፡ተስፋ፡ያደረግንባት፡ቀን፡ይህች፡ናት፤

ወረከብናሃ፡
ተድላ፡ደስታ፡ያገኘንባት፤

ወርኢናሃ፡
ደስታን፡ያየንባት፡ቀን፡ይህች፡ናት፡አሉ፤

፲፯፡ ፌ፡
ፍቄር፡እግዚአብሔር፡ማለት፡ነው፤

ገብረ፡እግዚአብሔር፡ዘሐለየ፡
እግዚአብሔር፡ያሰበውን፡አደረገ፤

ወፈጸመ፡ዘነበበ፤
የተናገረውን፡ፈጸመ፤

ዘአዘዘ፡እግዚአብሔር፡በመዋዕለ፡ትካት፡
እግዚአብሔር ፡ ቀድሞ ፡ ዘመን ፡ ያዘዘውን፡ፈጸመ፤

ወነሠተ፡
አጠፋት፤

ወኢምህከ፡
አልራራላትም፤

ወአስተፍሥሐ፡ጸላዕተኪ፡
ጠላቶችሽን፡ደስ፡አሰኘ፤

ወአልዓለ፡ቀርነ፡ፀርኪ፡ላዕሌኪ፡
የጠላቶችሽን ፡ ሥልጣን ፡ በአንቺ ፡ ላይ፡ከፍ፡ከፍ፡አደረገ፤

፲፰፡ ጻዴ፡
ጸድቅ፡እግዚአብሔር፡ማለት፡ነው፤

አውየወ፡ልቦሙ፡ኀበ፡እግዚአብሔር፡
ልቡናቸው ፡ ወደ ፡ እግዚአብሔር ፡ ጮኸ፤

ለዓረፋተ ፡ ወለተ ፡ ጽዮን ፡ ይወርድ ፡ አንብዕከሙ፡ከመ፡ውኂዝ፡መዓልተ፡ወሌሊተ፤
በመዓልትም፡በሌሊትም፡ዕንባችሁ፡በጽዮን፡ልጅ፡ቅጽሮች፡እንደ፡ፈሳሽ፡ይፈስሳል፤

ወኢትረከቢ፡ለኪ፡ዕረፍተ፡
ዕረፍት፡አታገኚም፤

ወኢታረምም፡ብንተ፡ዓይንኪ፡
የዓይንሽ ፡ ብሌኔ ፡ እንባን ፡ ከማፍሰስ ፡ ዝም፡አትልም፤

፲፱፡ ቆፍ፡
ቅሩብ፡እግዚአብሔር፡ማለት፡ነው፤

ተንሥኢ፡ወተፈሥሒ፡ሌሊተ፡
በቀዳሚት ፡ ሰዓት ፤ በመጀመሪያው ፡ ሰዓት ፡ በሌሊት ፡ ተነሥተሽ ፡ ደስ ፡ ይበልሽ፤

ከዓዊዮ፡ከመ፡ማይ፡ለልብኪ፡ቅድመ፡ገጹ፡ለእግዚአብሔር፡
ልቡናሽን ፡ በእግዚአብሔር ፡ ፊት ፡ እንደ ፡ ውሀ ፡ አፍሺው ፡ ማለት ፡ አሳዝኚው፤



አንሥኢ ፡ እደወኪ ፡ ኀቤሁ ፡ በእንተ ፡ ሕፃናትኪ፡እለ፡ኀልቁ፡በረሀብ፡
በረሀብ ፡ በቀጠና ፡ ስለ ፡ አለቁ ፡ ስለ ፡ ልጆችሽ ፡ ሰውነት ፡ እደ ፡ ልቡናሽን ፡ ወደ፡እርሱ፡አንሺ፤

በርእሰ፡ኵሉ፡ፍኖት፡
በየጎዳናው ፡ በሰው ፡ ሁሉ ፡ ራስ ፡ ቡሀነት፡ትወጣለች፤

፳፡ ሬስ፡
ርኡስ፡እግዚአብሔር፡ማለት፡ነው፤

ርኢ፡እግዚእ፡ወነጽር፡
አቤቱ፡መከራዬን፡እይ፡ተመልከት፤

መኑ፡ተቀረምኪ፡ከመዝ፡
እንደዚህ፡አድርገሽ፡ማንን፡በመከራ፡ለቀምሽ፡ማለት፡ማነን፡አጠፋሽ፤

ይበልዓኑ፡አንስት፡ፍሬ፡ከርሦን፡
አንተ፡ብትጣላን፡ነው፡እንጂ፡ሴቶች፡ልጆቻቸውን፡ይበሉ፡ነበር?

ወሐፃንያት፡እለ፡ያጠብዋ፤
ሞግዚቶችሺስ ፡ የሚያጠብዋቸውን ፡ ልጆች፡ይበሉ፡ነበር?

አው፡ይቀትሉኑ፡ካህነ፡ወነቢየ፡በመቅደሰ፡እግዚአብሔር፡
ከፉዎች፡ነገሥታትስ፡መምህሮችህ፡ነቢያት ፡ ካህናትን ፡ ይገድሉ ፡ ነበር? አንተ ፡ ብትጣላን ፡ አይደለምን? አንድም፡ይበልዓኑ፡አንስት፡አንተ፡ብትጣላን፡ነው፡እንጂ፡ሴቶች፡ልጆቻቸውን፡ይበላሉ? እኛንስ፡በምግባር፡በሃይማኖት ፡ የወለድኸን ፡ አይደለምን? ወሐፃንያት፡ሞግዚቶችስ፡የወለዷቸውን፡ይበላሉ? እኛንስ፡በመና፡በደመና ፡ ያሳደግኸን ፡ አይደለም ? አው፡ ይቀትሉኑ ፡ በጎዎች ፡ ነገሥታትስ ፡ በቤተ ፡ መቅደስ ፡ ነቢያት ፡ ካህናትን ፡ ይገድላሉ ? እኛስ ፡ ነቢያትህ፡ካህናትህ፡አይደለንም?

፳፩፡ ሳን፡
ስቡሕ፡እግዚአብሔር፡ማለት፡ነው፤

አስከብዎሙ፡ውስተ፡ምድር፡በአፍኣ፡
ከምድር ፡ አምበልብለው ፡ አስተ ኗቸው ፤ ወንዝ ፡ ሸጥ ፡ ሲያገኙ ፡ ደልድለው፡ይሔዱባቸዋልና፤

አዕሩግ፡ወሕፃናት፡
ሽማግሎች፡ሕፃናቱ፤

ወደናግልየ፡ወወራዙትየ፡
ቆናጅቱ፡ጎልማሶቼ፤

ወድቁ፡በኲናት፡
በጦር፡ጠፉ፤

ወቀተልከሙ፡በዕለተ፡መዓትከ፡
መዓትህን፡በአመጣህበት፡ቀን፡አጠፋሃቸው፤

ቀተልከ፡ወኢመሐከ፡
አጠፋህ፡አልራራህም፤

፳፪፡ ታው፡
ትጉህ፡እግዚአብሔር፡ማለት፡ነው፤

እጼውዕ፡አመ፡ዕለተ፡በዓል፡በኀበ፡ኀደርኩ፡እምዓዊድ፡
ከዞረት፡ከአደርኩበት፡ቦታ፡በዓለ፡ሰዊትን ፡ በዓለ ፡ ፋሲካን ፡ በአከበር ኩበት፡ቀን፡እጠራለሁ፤

ወኢኮነ፡በዕለተ፡መዓቱ፡ለእግዚአብሔር፡ዘይድኀን፡
እግዚአብሔር ፡ ተቆጥቶ ፡ መዓቱን ፡ በአመጣበት፡ቀን፡የሚድን፡የለም፤

ወዘይተርፍ፡
የሚቀር፡የለም፤

www.ethiopianorthodox.org

ዘአልሐቁ፡ወዘሐፀንኩ፡ፀርየ፡አሕለቅዎሙ፡
ያሳደግኋቸውን ፡ ጠላቶቼ ፡ አጠፋ
ዋቸው፤

## ምዕራፍ ፡ ፫ ፡
## ጉባዔ፤

፩፤ አሌፍ፡
አሐዱ፡እግዚአብሔር፡ማለት፡ነው፤
አነ ፡ ብእሲ ፡ ዘይሬኢ ፡ ተፅናሰ ፡ በበትረ ፡
መዓቱ፡፡
በበትረ፡መዓቱ፡ተመትቼ፡መከራን፡
የማይ፡እኔ፡ነኝ፤አንድም፡ዘእሬኢ፡
በበትረ ፡ መዓቱ ፡ ችግር ፡ በግን ፡
የምጠብቅ፡እኔ፡ነኝ፤

፪፤ ወነሥአኒ ፡ ወወሰደኒ ፡ ውስተ ፡
ጽልመት፡ዘአልቦ፡ብርሃን፡
ብርሃን፡ወደሌለበት፡ወደ፡አዘቅተ፡
ኰስህ፡ወሰደኝ፡ይላል፡ኤርምያስ፤
አንድም ፡ ተድላ ፡ ተደስታ ፡ ወደ ፡
ሌለበት ፡ ወደ ፡ ባቢሎን ፡ ወሰደኝ ፡
ይላል፡ትሩፍ፤

፫፤ ወሚጠ፡እዴሁ፡ኀቤየ፡ኵሎ፡ዕለተ፡
ሁልጊዜ፡እደ፡መዓቱን፡ወደ፡እኔ፡
መለሰ፤

፬፤ ወበልየ፡ሥጋየ፡ወማእስየ፡
ሰውነቴ፡በመከራ፡ተለዋወጠ፤
ወተቀጥቀጠ፡አዕፅምትየ፡
አጥንቴ፡በመከራ፡ተቀጠቀጠ፤

፭፤ ቤት፤
ባዕል፡እግዚአብሔር፡ማለት፡ነው፤
ሐነፀ፡ጥቅመ፡ላዕለ፡ርእስየ፡
በራሴ፡ላይ፡የመከራውን፡ግንብ፡ሠራ፡
ማለት፡መከራውን፡በእኔ፡ላይ፡አጸና፤

ወሦርሐ፡ፍኖተ፡ሕማም፡በላዕሌየ፡
የመከራው፡መገሳገሻ፡አደረገኝ፤

፮፤ ወውስተ፡ጽልመት፡አንበረኒ፡ከመ፡
ምውተ፡ትካት፡
እንደ፡ዱሮ፡ሬሳ፡በመቃብር፡አኖረኝ፤

፯፤ ወነደቀ፡ላዕሌየ፡
በእኔ፡ላይ፡መከራውን፡አጸና፤
ወኢይወጽእ፡
ከመከራው፡አልወጣም፤
ወአክበደ፡ብርከየ፡
ኰብሽ፡በሚባል፡በሽታ፡ጉልበቴን፡
አሳበጠ ፤ አንድም ፡ ብርትየ ፡ መከ
ራዬን፡አጸና፤

፰፤ ጋሜል፡
ግሩም፡እግዚአብሔር፡ማለት፡ነው፤
እጸርሕ፡ወአአወዩ፡
በመከራው፡ተይገፎ፡እጮሃለሁ፤
እስመ፡ተፈጸመ፡ጸሎትየ፡
ልመናዬ፡ተፈጽሟልና፤

፱፤ ዳሌጥ፡
ድልው፡እግዚአብሔር፡ማለት፡ነው፤
ወሐነፀ፡ፍኖትየ፡በኰኵሕ፡
ጐዳናዬን፡በጦር፡ከበበው፤
ወዐጸወ፡ፍኖትየ፡
ጐዳናዬን፡በጦር፡ዘጋ፤

፲፤ ድብ፡እንተ፡ትንዐ፡ውእቱ፡ሊተ፡
የሚያድን፡ተኵላ፡ግሥላ፡ሆነብኝ፡
ማለት፡አጠፋኝ፤
ወከመ ፡ አንበሳ ፡ ጽሚተ ፡ ዴገነኒ ፡ ወአሕ
ለቀኒ፡
አንበሳ ፡ ተሠውሮ ፡ ጊደርን ፡ እንዲ
ሰብር፡ተሠውሮ፡አጠፋኝ፤



፲፩፤ ወረሰየኒ፡ገዳመ፤
ከረድኤት ፡ ምድረ ፡ በዳ ፡ አደረገኝ፤
ከተድላ፡ከደስታ፡ብትልም፤

፲፪፤ ሄ፡
ህልው፡እግዚአብሔር፡ማለት፡ነው፤
ወሰቀ፡ቀስቶ፡
ቀስተ፡መዓቱን፡ሳበ፤
ወአቀመኒ፡ከመ፡መጠራ፡ለሐፅ፡
ለፍላፃ ፡ ትከሻን ፡ እንዲያቆሙለት ፡
በመከራ፡አቆመኝ፤

፲፫፤ ወነደፈኒ ፡ ውስተ ፡ ኵልያትየ ፡
በአሕፃሁ፡
ኵላሊቴን ፡ በጦር ፡ ወጋኝ ፡ ማለት ፡
ኵላሊቱን ፡ የተወጋ ፡ እንዳይድን ፡
የማይድን፡መከራ፡አመጣብኝ፤

፲፬፤ ወኮንኩ፡ሰሐቀ፡ለኵሉ፡ሕዝብየ፡
ለወገኖቼ፡ሁሉ፡መሳቂያ፡መዘበቻ፡
ሆንኩ፤
ወየሐልዩኒ፡ኵሎ፡አሚረ፡
ሁልጊዜ ፡ ዋይ ፡ ሸሸ ፡ ተበላሸ ፡
ይሉኛል፤

፲፭፤ ዋው፤
ዋሕድ፡እግዚአብሔር፡ማለት፡ነው፤
አጽገበኒ፡ኀምዘ፡
ኅምዘ፡መዓቱን፡አጠገበኝ፤
ወአርወየኒ፡ሐሞተ፡
ሐሞት ፡ አጠጣኝ ፡ ማለት ፡ ሐሞት ፡
መራራ ፡ ነው፤ መራራ ፡ መከራ ፡
አመጣብኝ፤

፲፮፤ ወሠበረኒ፡ስነንየ፡በኖፃ፡
ጥርሴን ፡ በአሸዋ ፡ ሠበረኝ ፡ ማለት ፡
ሥልጣኔን፡አጠፋ፤
ወአቅምሐኒ፡ሐመደ፤
አመድ፡አቃመኝ፡ማለት፡በመከራ፡
አጕሠቈለኝ፤

፲፯፤ ቀብፀት፡ነፍስየ፡ሰላመ፡
ሰውነቴ ፡ ተድላውን ፡ ደስታውን ፡
አጣች፤
ወረሣዕክዋ፡ለሠናይትየ፡
ተድላዬን፡ደስታዬን፡ዘነጋኋት፤

፲፰፤ ወኃጕልኩ ፡ ተስፋየ ፡ ወትውክ
ልትየ፤በኀበ፡እግዚአብሔር፡
ከእግዚአብሔር ፡ ዘንድ ፡ ተስፋዬን ፡
አለኝታዬን፡አጣሁ፤

፲፱፤ ዛይ፡
ዝኩር፡እግዚአብሔር፡ማለት፡ነው፤
ተዘከር፡ተፅናስየ፡ወተሰዶትየ፡
ችግሬን ፡ በመከራው ፡ መሰደዴን ፡
አስብ፤
ወምረተ፡ኅምዝየ፡
የመከራዬን፡ፅናት፡አስብ፤አንድም፡
ወምሕረተ ፡ ሕዝብየ፤ የወገኖቼን ፡
ይቅርታ፡አስብ፤

፳፤ ወአንበዘት፡ነፍስየ፡በላዕሌየ፡
በእኔ ፡ ላይ ፡ ያለች ፡ ሰውነቴ ፡ አእም
ሮዋን፡አጣች፤

፳፩፤ ወአነብር፡ውስተ፡ልብየ፡ትካዘ፡
በልቡናዬ፡ኃዘንን፡አኖራለሁ፤
በእንተ፡ዝንቱ፡እትዔገሥ፡
ስለዚህ ፡ ነገር ፡ መከራውን ፡ እታገ
ሣለሁ፤

፳፪፤ ሔት፤
ሕያው፡ሕይወት፡ማለት፡ነው፤
ምሕረተ፡እግዚአብሔር፡እስመ፡ኢኀልቀ፡
ወኢተፈጸመ፡ሣህሉ፡ሐዳሳት፡ለለጽባሑ፤
ጢት፡ማታ፡እንግዳ፡እንግዳ፡ሥራ፡
ነገር ፡ ይሠራል፤ እንጂ ፡ የእግዚአ
ብሔር፡ቸርነቱ፡ይቅርታው፡አልተፈ
ጸመምና፡እትዔገሥ፡መከራውን፡እታ
ገሣለሁ፤

www.ethiopianorthodox.org

፳፫፤ በዝኁ፡ጽድቅከ፡ክፍልየ፡እግዚአ ብሔር፡ትቤ፡ነፍስየ፡
እድል ፡ ፈንታዬ ፡ እግዚአብሔር ፡ ሰውነቴ ፡ ቸርነትህ ፡ በዛ ፡ አለች ፤ አንድም፡ብዝኁ፡ጽድቅከ፡ቢል፡ለቸር ነትህ፡ብዛት፡ዕድል፡ፈንታዬ፡ጽዋ፡ ተርታዬ ፡ ነው ፡ አለች ፤ ከአሌፋቱ ፡ እያሳለፈ፡ይሠራል፤

፳፬፤ በእንተ፡ዝንቱ፡ጸናሕኩ፡
ስለዚህ ፡ ነገር ፡ ይቅርታህን ፡ ደጅ ፡ ጠናሁ፤

፳፭፤ ጤት፡
ጠቢብ፡እግዚአብሔር፡ማለት፡ነው፤
ኄር፡እግዚአብሔር፡ለእለ፡ይትዔገሥዎ፡
ለፈተና ፡ ብሎ ፡ መከራ ፡ ቢያመጣ ባቸው ፡ መከራ ፡ እንጂ ፡ ለወዳጆቹ ፡ ነው፡ ብለው ፡ መከራውን ፡ ለሚታ ገሡ፡ ሰዎች ፡ እግዚአብሔር ፡ ቸር ፡ ነው፤

፳፮፤ ለነፍስ ፡ እንተ ፡ ተኀሥሥ ፡ በሠናይ፡ ወትትዔገሥ ፡ ወታረምም ፡ ለመድ ኃኒተ፡እግዚአብሔር፡
የእግዚአብሔርን ፡ ድኅነት ፡ ለማ ግኘት ፡ በበጎ ፡ ነገር ፡ ፀንታ ፡ መከራውን፡ ለምትታገሥ ፡ ዝም ፡ ለምትል፡ሰውነት፡ቸር፡ነው፤

፳፯፤ ሠናይ ፡ ለብእሲ ፡ ሶበ ፡ ይነሥእ ፡ አርዑቶ፡እምንእሱ፤
ከሕፃንነቱ ፡ ጀምሮ ፡ ሕገ ፡ እግዚአብ ሔርን ፡ የያዘ ፡ ሰው ፡ በጎ ፡ ነው ፡ እንደ ፡ ሳሙኤል፤

፳፰፤ ዮድ፡
የማነ፡እግዚአብሔር፡ማለት፡ነው፤
ይነብር፡ባሕቲቱ፡
ከኃጢአት፡ከጣዖት፡ተለይቶ፡ቢኖር፤
ወይፃሙ፡
ለበጎ፡ነገር፡ቢደክም፤
ሶበ፡አንሥኡ፡ላዕሌሁ፡
ነገር፡ቢያነሡበት፤

፳፱፤ ይወዲ፡ውስተ፡መሬት፡አፉሁ፡
አፉ፡ዝም፡የሚል፤
ዮጊ፡ቦ፡ተስፋ፡ይመይጥ፡መልታሕቶ፡ለዘይ ጸፍዖ፡
ወይም፡ተስፋውን፡አገኘለሁ፡ብሎ፡ ቀኙን ፡ ቢጸፋት ፡ ግራውን ፡ የሚ መልስ፡ቢኖር፤

፴፤ ወይጸግብ፡ዕዕለተ፡
ስድብን ፡ ቢታገሥ ፡ በጎ ፡ ነው ፤ አንድም፡ ሠናይ ፡ ለብእሲ ፡ ሶበ ፡ ይነሥእ ፡ አርዑቶ ፡ እምንእሱ ፡ ከሕፃ ንነቱ ፡ ጀምሮ ፡ ሕጉን ፡ ቢጠብቅ ፤ ይነብር፡ባሕቲቱ፡ከዘለዓለም፡ተድላ፡ ደስታ ፡ ተለይቶ ፡ ቢኖር ፤ ወይፃሙ ፡ በምግባር ፡ በትሩፋት ፡ ቢደክም ፡ ቢኖር፡ በጎ ፡ ነው ፤ እንደ ፡ አባ ፡ ብሶይ፡ ሶበ ፡ አንሥኡ ፤ ነገር ፡ ቢያነሡበት ፤ ይወዲ ፡ ውስተ ፡ አፉሁ ፡ ዝም ፡ ቢል ፡ ዮጊ ፤ አንድም ፡ ተስፋ ፡ ይመይጥ ፡ ወይም፡አለኝታውን፡አገኛለሁ፡ብሎ፡ ቀኙን ፡ ቢጸፋት ፡ ግራውን ፡ የሚ መልስ፡ ቢኖር ፤ ወይጸግብ ፡ ስድብን ፡ ቢታገሥ፡በጎ፡ነው፤

፴፩፤ ካፍ፡
ከሀሊ፡እግዚአብሔር፡ማለት፡ነው፤
እስመ ፡ ኢይገድፎሙ ፡ እግዚአብሔር ፡ ለዓለም፡
እግዚአብሔር፡ለዘለዓለም፡በመከራ፡ አይጥላቸውምና፤

፴፪፤ እስመ ፡ ዘአሕመመ ፡ ይሠሃል ፡ በከመ፡ብዝኃ፡ምሕረቱ፡



እንደ ፡ ይቅርታው ፡ ብዛት ፡ መጠን ፡ መከራ ፡ ያጸናበትን ፡ ሰው ፡ ይቅር ፡ የሚል፡ስለሆነ፤

፴፫፤ እስመ፡ኢተቈጥዐ፡ልቡ፡
ልቡናው፡አልተበሳጨምና፤
ወኢሐመ፡በደቂቀ፡ዕጓለ፡እመሕያው፡
በሰው ፡ ልጆች ፡ መከራ ፡ አልተቀበ ለምና፤

፴፬፤ ከመ ፡ ይኅሥር ፡ በታሕተ ፡ እገሪሆሙ፡በኵሉ፡ኅሡራነ፡ምድር፡
ጐስቋሎች፡በሚሆኑ፡ኃጥአን፡ፊት፡ ከጠላታቸው ፡ እግር ፡ በታች ፡ ይጐሰቍል፡ዘንድ፤

፴፭፤ ላሜድ፡
ልዑል፡እግዚአብሔር፡ማለት፡ነው፤
ከመ፡ይሚጥ፡ፍትሐ፡ብእሲ፡በቅድመ፡ገጸ፡ ልዑል፡ይደይ፡በእሲ፡ውስተ፡ኵነኔ፡እግዚአ ብሔር፡ዘኢአዘዘ፤
ይሚጥና፡ይደይ፡አንድ፡ወገን፡ነው፤ ሰው ፡ እግዚአብሔር ፡ ያላዘዘውን ፡ ሲፈርድ፡ጊዜ፡የሰውን፡ፍርድ፡ወደ፡ እግዚአብሔር ፡ ይመልስ ፡ ዘንድ ፤ አንድም ፡ ለማውጣት ፡ ሰው ፡ እግዚአ ብሔር ፡ ያላዘዘውን ፡ በፈረደ ፡ ጊዜ ፡ መከራውን ፤ ይደይ ፡ ውስተ ፡ ኵነኔ ፤ ሰውን ፡ ለማጥፋት ፡ የሰውን ፡ ፍርድ ፡ ወደ፡እግዚአብሔር፡ይመልስ፡ዘንድ፡ ልቡናው፡አልተበሳጨምና፤ እስመ፡ዘአሕመመ፡ይሠሃል፡መከራ፡ ያጸናበትን፡ይቅር፡የሚል፡ስለሆነ፡ እስመ፡ኢይገድፎሙ፡አንድ፡ጊዜ፡ ቢጥላቸው ፡ ለዘለዓለም ፡ እንደጣላ ቸው፡አይቀርምና፡ሰው፡ከሕፃንነቱ፡ ጀምሮ፡ሕገ፡እግዚአብሔርን፡ቢይዝ፡ በጎ፡ነው፡ብለህ፡እሠር፤

፴፮፤ሜም፡
ምዑዝ፡እግዚአብሔር፡ማለት፡ነው፤
መኑ ፡ ዘይቤ ፡ ዘይከውን ፡ እግዚአብሔር ፡ ዘኢአዘዘ፡
እግዚአብሔር ፡ ያላዘዘው ፡ መከራ ፡ ይደረጋል፡ያለ፡ማነው?

፴፯፤ ወእምአፈ ፡ ልዑል ፡ ዘኢወጽአ ፡ እኩይኒ፡ወሠናይኒ፡
መከራውም ፡ ተድላውም ፡ ደስታ ውም ፡ ያለእግዚአብሔር ፡ ትእዛዝ ፡ የማይመጣ፡ስለሆነ፤

፴፰፤ለምንት፡ያንጐረጕር፡ሰብእ፡እንዘ፡ ሕያው፡ብእሲ፡በእንተ፡ኃጢአቱ፤
ሰው ፡ በሕይወቱ ፡ ሳለ ፡ መከራ ፡ ቢመጣበት፡በኃጢአቱ፡ለምን፡ያንጐ ራጕራል፤

፴፱፤ኖን፡
ኖላዊ፡ንጉሥ፡እግዚአብሔር፡ማለት ነው፤
ንሕትት፡ፍኖተነ፡ወንኅሥሥ፡
ሥራችንን፡እንመርምር፤
ወንትመየጥ፡ኀበ፡እግዚአብሔር፡
በአምልኮት ፡ ወደ ፡ እግዚአብሔር ፡ እንመለስ፤

፵፤ናንሥእ፡ልበነ፡ወእደዊነ፡ኀበ፡እግዚአ ብሔር፡ሰማየ፡
በሰማይ፡ወዳለ፡ወደ፡እግዚአብሔር፡ ቃላችንን፡ልቡናችንን፡እናንሣ፤

፵፩፤ንሕነ፡አበስነ፡ወጌገይነ፡
እኛ፡ፈጽመን፡በደልን፤
ወአንተኒ፡ኢመሐከነ፡
አንተም፡አልራራኅልንም፤

፵፪፤ሳምኬት፡
ሰፋኒ፡እግዚአብሔር፡ማለት፡ነው፤

www.ethiopianorthodox.org

ክደንከነ፡በመዓት፡ወሰደድከነ፡
በመከራ ፡ ሸፈንኸን ፡ ከሀገራችን ፡ አስ ወጥተህ፡ሰደድከን።

ወቀተልከነ፡
አጠፋኸን።

ወኢመሐከነ፡
አልራራኅልንም።

፵፬፡ ጸለልከነ፡በደመና፡
በመከራ፡ሸፈንኸን።

እምወጺእ ፡ ለምዕራግ ፡ ጸሎትነ ፡ ከመ ፡ ንሕምም፡ወከመ፡ኢንርአይ፡
ተድላ ፡ ደስታ ፡ እንዳናይ ፡ ጸሎታችን፡ ወደሚያርግበት ፡ ወደ ፡ ኢየሩሳሌም ፡ ከመውጣት ፡ በመከራ ፡ ሸፈንከን ፡ ኢንሕምም ፡ ወከመ ፡ ንርዓይ ፡ ቢል ፡ መከራ ፡ እንዳንቀበል፡ ተድላ ፡ ደስታ ፡ እናይ ፡ ዘንድ ፡ ለምዕራግ ፡ ጸሎትነ ፡ ጸሎታችን ፡ ወደሚያርግበት ፡ ወደ ፡ ኢየሩሳሌም ፡ ከመውጣት ፡ በመከራ ፡ ሸፈንኸን ፡ አንድም ፡ ከመ ፡ ንሕምም፡ ብለህ፡ወደታች፡እሠር።

፵፭፡ ወአንበርከነ፡ማዕከለ፡አሕዛብ፡
በአሕዛብ ፡ መካከል ፡ በባቢሎን ፡ አኖርኸን ፡ አንድም ፡ ማካፈል ፡ ነው ፡ ከመ ፡ ንሕምም ፡ መከራ ፡ እንቀበል ፡ ዘንድ ፡ ጸለልከነ ፡ ላለው ፡ ወከመ ፡ ኢንርዓይ ፡ ተድላ ፡ ደስታ ፡ እንዳናይ ፡ አንበርከነ፡ላለው።

፵፮፡ ፄ፡
ዓቢይ፡እግዚአብሔር፡ማለት፡ነው።

ከሠቱ፡አፉሆሙ፡ላዕሌነ፡ኵሉ፡ዐርነ፡
ጠላቶቻችን ፡ ሁሉ ፡ በእኛ ፡ ላይ ፡ አፋቸውን፡ከፈቱ።

፵፯፡ ፍርሃት፡ወረዓድ፡አኀዘነ፡
ፍርሃት፡እንቅጥቅጥ፡ያዘን።

፵፰፡ ፈለገ፡ማይ፡ውኅዘ፡እምአዕይንቲነ፡
ከዓይናችን፡የዕንባ፡ጐርፍ፡ፈሰሰ።

በእንተ፡ቅጥቃጤሃ፡ለወለተ፡ሕዝብየ፡
የወገኔ ፡ ልጅ ፡ በመከራ ፡ ስለተቀጠቀጠች።

፵፱፡ፄ፡
ፍቁር፡እግዚአብሔር፡ማለት፡ነው።

ዓይንየ፡ተደፍነት፡
ዓይኔ፡በዕንባ፡ተቀበረች።

ወኢያረምም፡እንከ፡እምአልዕሎ፡
እንግዲህ ፡ ወዲህ ፡ ቃሌን ፡ ከፍ ፡ ከፍ፡ አድርጌ፡ከማልቀስ፡ዝም፡አልልም።

፶፡ እስከ ፡ ይሬኢ ፡ እግዚአብሔር ፡ እምሰማይ፡
እግዚአብሔር ፡ መከራዬን ፡ ከሰማይ ፡ እስኪያይልኝ፡ድረስ።

፶፩፡ ዓይንየ ፡ አሕመሞ ፡ ለነፍስየ ፡ በእንተ፡ ኵሉ፡ነፍሰ፡አዋልደ፡ሀገርየ፡
ለሀገሬ ፡ ልጆች ፡ ሁሉ ፡ ዓይኔ ፡ ዕንባን፡ አፈሰሰ።

፶፪፡ ጻዴ፡
ጻድቅ፡እግዚአብሔር፡ማለት፡ነው።

ንዒወ፡ነዓወኒ፡ዐር፡ከመ፡ዖፍ፡
ጠላት፡እንደ፡ዖፍ፡አደነኝ።

፶፫፡ ወቀተሉ ፡ ሕይወትየ ፡ በከንቱ ፡ በውስተ፡አዘቅት፡
ሳልበድላቸው ፡ በከንቱ ፡ በአዘቅት ፡ ኵስሕ፡ሰውነቴን፡ለወጡት።

ወከደኑኒ፡ዕብነ፡
ደንጊያ ፡ ገጠሙብኝ ፡ ደንጊያ ፡ ገጥመውበታልና።

፶፬፡ ተክዕወ፡ማይ፡ላዕለ፡ርእስየ፡
በቁሙ ፡ እንዲያረጥበው ፡ ብለው ፡ ውሀ፡አፍስሰውበታል።



እቤ፡ተኀደጉ፡እምኔሁ፡
ከባለሟልነት ፡ ወጣሁ ፡ አለ ፡ ኤርምያስ ፡ አንድም ፡ ወቀተሉ ፡ ትሩፍ ፡ ሳልበድላቸው፡በባቢሎን፡ሰውነቴን፡ አጠፉ ፡ ወከደኑኒ ፡ መከራ አጸኑብኝ ፡ ተክዕወ፡ማይ፡ዕንባዬ፡በዝቶ፡ፈሰሰ፡ ማለት ፡ መከራው ፡ በዝቶ ፡ መጣብኝ ፡ ዕቤ ፡ ተኀደጉ ፡ ከእግዚአብሔር ፡ ተለየሁ፡ይላል።

፶፭፡ ቆፍ፡
ቅሩብ፡እግዚአብሔር፡ማለት፡ነው።

ጸዋዕኩ፡ስመከ፡እምግብ፡ታሕቲት፡
ኤርምያስ ፡ በአዘቅተ ፡ ኵስሕ ፡ ሳለሁ፡ ስምህን ፡ ጠራሁ ፡ ይላል ፡ አንድም ፡ በባቢሎን ፡ ሳለሁ ፡ ስምህን፡ ጠራሁ ፡ ይላል፡ትሩፍ።

፶፮፡ ወሰማዕከኒ፡ቃልየ፡
ልመናዬን፡ሰማኸኝ።

ወኢትሚጥ፡ዕዝነከ፡እምነ፡ስዕለትየ፡
ጆሮህን ፡ ልመናዬን ፡ ከመስማት ፡ አትመልስ።

፶፯፡ ቀረብከ፡በዕለተ፡እጼውዓከ፡
በለመንኩህ ፡ ጊዜ ፡ ቀረብኸኝ ፡ አንድም፡ቅረብ፡ቢል፡በለመንኩህ፡ጊዜ፡ ቅረብ።

ወትቤለኒ፡ኢትፍራህ፡
አትፍራ፡አልከኝ።

፶፰፡ ሬስ፡
ርኡስ፡እግዚአብሔር፡ማለት፡ነው።

ኰነንከ፡እግዚኦ፡ኵነኔ፡ነፍስየ፡
አቤቱ፡የሰውነቴን፡ፍርድ፡ፈረድህ።

ወቤዘውከ፡ሕይወትየ፡
ሰውነቴን፡አዳንህ።

፶፱፡ ርኢ ፡ እግዚኦ ፡ ኵሎ ፡ ዘይመከሩ ፡ ላዕሌየ፡
አቤቱ ፡ በእኔ ፡ ላይ ፡ የሚመክሩትን ፡ ሁሉ፡እይ፡ተመልከት።

ፍታሕ፡ፍትሕየ፡
ፍርዴን፡ፍረድ።

፷፡ ርኢ፡ኵሎ፡ተበቅሎቶሙ፡
እኔን ፡ መበቀላቸውን ፡ እይ ፡ ተመልከት።

ወኵሎ፡ሕሊናሆሙ፡ብየ፡
በእኔ ፡ ላይ ፡ ያሰቡትን ፡ ክፉ ፡ ሐሳባቸውን፡ሁሉ፡እይ፡ተመልከት።

፷፩፡ ሳን፡
ስቡሕ፡እግዚአብሔር፡ማለት፡ነው።

ሰማዕከ፡ኵሎ፡ዕዕለቶሙ፡እግዚኦ፡
አቤቱ፡ስድባቸውን፡ሁሉ፡ሰማህ።

ወኵሎ፡ሕሊናሆሙ፡ላዕሌየ፡
በእኔ ፡ ላይ ፡ ያሰቡትን ፡ ክፉ ፡ ሐሳባቸውንም፡እይ፡ተመልከት።

፷፪፡ ወዘአኖሙ ፡ ከናፍሪሆሙ ፡ ብየ ፡ ኵሎ፡ዕለተ፡
ሁልጊዜ ፡ በእኔ ፡ ላይ ፡ ከንፈራቸውን፡ ያነቃነቁትን፡እይ፡ተመልከት።

፷፫፡ ንበረቶሙ፡ወተንሥኦቶሙ፡ርኢ፡
ከኢየሩሳሌም ፡ መውጣታቸውን ፡ በባቢሎን፡መኖራቸውን፡አስብ።

አነ፡ማኅሌቶሙ፡
እኔ ፡ መጫወቻቸው ፡ ነኝ ፡ ዋይ ፡ ሸሸ፡ ተበላሸ፡እያሉ።

፷፬፡ ታው፡
ትጉህ፡እግዚአብሔር፡ማለት፡ነው።

ፍድዮሙ፡በከመ፡ምግባረ፡እደዊሆሙ፡
እንደ ፡ እጃቸው ፡ ሥራ ፡ መጠን ፡ ፍዳውን፡አምጣባቸው።

www.ethiopianorthodox.org

ወስድዶሙ፡በመዓትከ፡
በመዓትህ፡ከሀገራቸው፡አስወጥተህ፡ ስደዳቸው፤

፷፮፤ ወአጥፍኦሙ፡እምታሕተ፡ሰማይ፡
ከሰማይ ፡ በታች ፡ ካለ ፡ ከዚህ ፡ ዓለም፡ አጥፋቸው፤

እግዚኦ፡ሀቦሙ፡በከመ፡እከየ፡ልቦሙ፡
አቤቱ ፡ እንደ ፡ ልቡናቸው ፡ ክፋት ፡ መጠን፡መከራ፡አምጣባቸው።

## ምዕራፍ ፡ ፬ ፤

፩፤ አሌፍ፡
አሐዱ፡እግዚአብሔር፡ማለት፡ነው፤

እፎ፡ተጸልዓ፡ወርቅ፡ሠናይ፡
ያማረ ፡ የተወደደ ፡ ወርቅ ፡ እንዴት ፡ ተጠላ?

ወተመንነ፡ብሩር፡
ብርስ፡እንዴት፡ተናቀ?

ወተዘርወ ፡ ዕንቍ ፡ ቅዱስ ፡ ውስተ ፡ ኵሉ ፡ ፍኖት፡
የከበረ ፡ ዕንቍስ ፡ በየጐዳናው ፡ እንዴት፡ ተበተነ ? አርበኛ ፡ በሰልፍ ፡ ጊዜ ፡ ለግዳጅ ፡ ለምርኮ ፡ ሰውን ፡ ይፈልጋል፡እንጂ፡ወርቅ፡ብር፡አይፈ ልግምና፤ አንድም ፡ እፎ ፡ ተፀልአ ፤ ወርቅ፡ሠናይ፤
ንጉሡ፡እንዴት፡ተጠላ፤ወተመንነ፤ ሕዝቡስ፡እንዴት፡ተናቀ፤ወተዘርወ፤ የከበረ ፡ ሊቀ፡ ካህናቱ ፡ በጐዳና ፡ እንዴት፡ተማረከ፤

፪፤ ቤት፡
ባዕል፡እግዚአብሔር፡ማለት፡ነው፤

ደቂቀ፡ጽዮን፡ክቡራን፡ተሠይጡ፡በወርቅ፡
የከበሩ ፡ የጽዮን ፡ ልጆች ፡ በወርቅ ፡ ተሸጡ፤

እፎ፡ኮኑ፡ከመ፡ንዋየ፡ልሕኵት፡ግብረ፡እደ፡ ለብሐዊ፡
የሸክላ ፡ ሠሪ ፡ እጅ ፡ እንደሠራው ፡ እንደ፡ ብርሌ ፡ እንደ ፡ ብርጭቆ ፡ እንዴት፡ሆኑ፡ማለት፡ያ!እንዲሸጥ፡ እንዴት ፡ ተሸጡ ? ፡ ያ ! እንዲሠበር፡ እንዴት፡ተሠበሩ?

፫፤ ጋሜል፡
ግሩም፡እግዚአብሔር፡ማለት፡ነው፤

አክይስትኒ፡አጥበዋ፡ዕጐሊሆን፡
እባቦችስ ፡ እንኳ ፡ ልጆቻቸውን ፡ አጠቡ፤

አዋልደ፡ሕዝብየሰ፡ከመ፡አዕዋፍ፡በውስተ፡ ገዳም፡
የወገኖቼ፡ልጆች፡ግን፡በምድረ፡በዳ፡ እንደ፡ሰጐን፡ሆኑ፡አለ፤ያች፡ጥላ፡እን ድትሔድ ፡ ልጆቻቸውን ፡ ጥለው ፡ ሔዱ፤

፬፤ ዳሌጥ፡
ድልው፡እግዚአብሔር፡ማለት፡ነው፤

ጠግዓ ፡ ልሳነ ፡ ሕፃን ፡ ውስተ ፡ ጕርዔሁ፡ በጽምዕ፡
የሕፃኑ፡አንደበት፡ከጕረሮው፡ጋራ፡ በጥም፡ተጣጋ፤ልሳነ፡ሐፃኒት፡ቢል፡ የሞግዚት፡አንደበቷ፡ተጠማ፤

ወሕፃናት፡ሰአሉ፡ኅብስተ፡
ልጆች፡እህል፡ለመኗት፤

ወአልቦሙ፡ኅብስት፡ወኢረከቡ፡
የምትሰጣቸው ፡ አጣች ፤ ወኢረከቡ፡ አላገኙም፤አንድም፡ጠግዓ፡የሐፃኒት፡ የእመቤታችን ፡ አንደበት፡ በጥም ፡ ተያዘ ፤ ወሕፃናት ፡ ዮሴፍ ፡ ሰሎሜ፡ እህል ፡ ለመንዋት ፤ ወአልቦሙ ፡ የም ትሰጣቸው ፡ አጣች ፡ ወኢረከቡ ፡ አላገኙም፤



፭፤ ሄ፡
ህልው፡እግዚአብሔር፡ማለት፡ነው፤

እለ፡ይሴሰዩ፡ሲሳየ፡ማሰኑ፡በውስተ፡ፍኖት፡
ምግብን፡የሚመገቡ፡ሰዎች፡በጎዳና፡ ጠፉ፤

ወደፈኖሙ፡መሬት፡
መሬት፡ቀበራቸው፤

፮፤ ዋው፡
ዋህድ፡እግዚአብሔር፡ማለት፡ነው፤

ዐበየት፡ኃጢአታ፡ለወለተ፡ሕዝብየ፡እምኃ ጢአተ ፡ ሰዶም ፡ እንተ ፡ ተገፍአት ፡ ፍጡነ ፡ እንዘ፡ኢይፃምዉ፡ዕደው፡ባቲ፡
ወንዶች ፡ ሳይደክሙባት ፡ ፈጥና ፡ ከጠፋች፡ከሰዶም፡ኃጢአት፡ይልቅ፡ የወገኔ ፡ ልጅ ፡ ኃጢአት ፡ በዛ፤ እንዘ ፡ ኢይፃምዉ ፡ አለ ፡ በእሳት ፡ ነውና ፡ የጠፋች ፤ አንድም ፡ እንዘ ፡ ኢይፃ ምዉን፡ለእስራኤል፡ስጥ፤ሰዎች፡ሳይ ደክሙባት፡የጠፋች፡የወገኔ፡ልጅ፡ ኃጢአት፡ከሰዶም፡ኃጢአት፡ይልቅ፡ በዛ፤
እንዘ ፡ ኢይፃምዉ ፡ አለ ፡ ባኡ ፡ ከለዳ ውያን ፡ ወዌውውዎሙ ፡ ለዕብራ ውያን፡ብሎ፡በሩን፡ከፍቶ፡መልአኩ፡ አስገብቶዋቸዋልና፤

፯፤ዛይ፡
ዝኩር፡እግዚአብሔር፡ማለት፡ነው፤

ፃዕደዉ ፡ ቅዱሳኒሃ ፡ እምበረድ ፡ ወፃዕደዉ፡ እምሀሊብ፡
የኢየሩሳሌም፡ቅዱሳኖቿ፡እስራኤል፡ ከበረድ ፡ ከወተት ፡ ይልቅ፡ ንጹሐን፡ ሆኑ፤

ወቴሑ ፡ ፈድፋደ ፡ እምዕንቈ ፡ ሰንፔር ፡ በፀዓቶሙ፡
ከባቢሎን ፡ በወጡ ፡ ጊዜ ፡ ሰንፔር ፡ ከሚባል ፡ ዕንቍ ፡ ይልቅ ፡ ንጹሐን ፡ ሆኑ።

፰፤ ሔት፡
ሕያው፡ሕይወት፡ማለት፡ነው፤

ጸልመ፡እምነ፡ሕመት፡ራእዮሙ፡
ከዚያ ፡ አስቀድሞ ፡ መልካቸው ፡ ከከሰል፡ይልቅ፡ጠቆረ፤
ወኢተአውቀ፡በአፍአ፡ፍኖቶሙ፡
ከኢየሩሳሌም ፡ በአፍአ ፡ (በውጭ) ፡ ላሉ፡አሕዛብ፡መውጣታቸው፡አልታ ወቀም፤

ወቈቍዓ፡ማዕሰሙ፡በዲበ፡አዕጽምቲሆሙ፡
በአጥንታቸው ፡ ላይ ፡ ያለ ፡ ቁርበ ታቸው፡ቋ፡ቋ፡አለ፤

ወየብሰ፡ከመ፡ዕፅ፡
እንደ ፡ እንጨት ፡ ደረቀ ፤ አንድም ፡ ፃዕደዉ ፡ ቅዱሳኒሃ ፡ እምበረድ ፡ ወፃዕደዉ ፡ እምሀሊብ ፤ የቤተ ፡ እስራኤል ፡ ቅዱሳኖቿ ፡ ሠለስቱ ፡ ደቂቅ፡ ከበረድ፡ ከሀሊብ ፡ (ከወተት)፡ ይልቅ ፡ ነጭ ሆኑ ፤ ወቴሐ ፡ ከእሳት፡ በወጡ ፡ ጊዜ ፡ ሰንፔር ፡ ከሚባል ፡ ዕንቍ፡ ይልቅ ፡ ነጭ፡ ሆኑ ፤ ጸልመ ፡ እምነ፡ሕመት፡ከእቶነ፡እሳት፡ከመው ጣታቸው ፡ አስቀድሞ ፡ መልካቸው ፡ ከከሰል፡ይልቅ፡ጠቈረ፤ወኢተዐውቀ፡ በአፍአ፡ከእቶነ፡እሳት፤
በአፍአ፡(በውጭ)፡ላሉ፡ሰዎች፡ሕይ ወታቸው ፡ ድኅነታቸው ፡ አልታ ወቀም ፤ ወቈቍዓ ፡ በአጥንታቸው ፡ ላይ፡ያለ፡ቁርበታቸው፡(ቆዳቸው)፡ቋ፡ ቋ ፡ አለ ፤ ወየብሰ ፡ ምትሐት ፡ አይደ ለምና ፡ አይተው ፡ በድንጋጤ ፡ ሰውነ ታቸው ፡ እንደ ፡ እንጨት ፡ ደረቀ ፤ አንድም ፡ ፃዕደዉ ፡ ቅዱሳኒሃ ፡ የቤተ ፡

www.ethiopianorthodox.org

ክርስቲያን ፡ ቅዱሳኖቿ ፡ እለ ፡ አርሳ
ንዮስ ፡ ከበረድ፡ ከሀሊብ (ከወተት) ፡
ይልቅ ፡ ንጹሐን ፡ ሆኑ ፤ ወቄሑ ፡
ከክብር፡ ወደ ፡ ክብር ፤ ከማዕረግ ፡ ወደ
ማዕረግ፡ በወጡ ፡ ጊዜ ፡ ጸልመ ፡
መልካቸው ፡ በገድለ ፡ ሥጋ ፡ ጠቈረ ፤
ወኢተዐውቀ፡ ከክብር ፡ ከማዕርግ ፡
በአፍአ ፡ (በውጭ) ፡ ላሉ ፡ ሰዎች ፡ ድኅነ
ታቸው፡ አልታወቀም ፤ ወቈቈዓ ፡ ቈር
በታቸው ፡ በአጥንታተቸው ፡ ላይ፡ ቋ ፡
ቋ ፡ አለ ፤ ወየብሰ ፡ ከመ ፡ ዕፅ ፡ እንደ ፡
እንጨት ፡ ጠቈረ ፤

፱፤ ጤት፤
ጠቢብ፡እግዚአብሔር፡ማለት፡ነው፤
ሐየሱ ፡ ቅቱላን ፡ በኲናት ፡ እምቅቱላን ፡
በረኃብ፤
በረኃብ ፡ ከሞቱት ፡ ሰዎች ፡ ይልቅ ፡
በጦር፡የሞቱ፡ሰዎች፡በለጡ፤
ወሐሩ ፡ እንዘ ፡ ርጉዛን ፡ በትእዛዘ ፡ እግዚአ
ብሔር፤
በእግዚአብሔር ፡ ትእዛዝ ፡ በረኃብ ፡
ጦር፡ተወግተው፡ተማርከው፡ሔዱ፤

፲፤ ዮድ፤
የማን፡እግዚአብሔር፡ማለት፡ነው፤
እደዊሆን ፡ ለአንስት ፡ መሐርያት ፡ አብሰላ ፡
ዕጕሊሆን፤
ርኅሩኅት ፡ የነበሩ ፡ የሴቶች ፡ እጆች ፡
ልጆቻቸውን፡ቀቀሉ፤
ወኮንዎን ፡ ሲሳዮን ፡ በቅጥቃጤሃ ፡ ለወለተ፡
ሕዝብየ፤
የወገኔ፡ልጅ፡በመከራ፡ስለጠፋች፡ስለ
ተቀጠቀጠች፡ምግባቸውን፡ሆኗቸው፤

፲፩፤ ካፍ፤
ከሐሊ፡እግዚአብሔር፡ማለት፡ነው፤
ፈጸመ፡እግዚአብሔር፡መዓቶ፤
እግዚአብሔር፡መዓቱን፡ፈጸመ፤
ወከዐወ፡መቅሠፍቶ፤
መቅሠፍቱን፡አብዝቶ፡አመጣ፤
ወአንደደ፡እሳተ፡ላዕለ፡ጽዮን፤
በጽዮን፡ላይ፡መከራን፡አመጣ፤
ወበልዐት፡መሠረታቲሃ፤
ሥር፡መሠረቷን፡አጠፋች፤ አንድም፡
ጦር፡ኃያላኗን፡መኳንንቷን፡አጠፋች፤

፲፪፤ ላሜድ፤
ልዑል፡እግዚአብሔር፡ማለት፡ነው፤
ኢአምኑ፡ነገሥተ፡ምድር፤
የእስራኤል፡ነገሥታት፡አላመኑም፤
ወኵሎሙ፡እለ፡ይነብሩ፡ውስተ፡ዓለም፤
በዚህ፡ዓለም፡የሚኖሩ፡ሰዎች፡ሁሉ፤
ከመ፡ይበውእ፡ፀር፡ወጸላኢት፡አንቀጸ፡ኢየሩ
ሳሌም፤
ፀር፡የጊዜው፡ጸላኢት፡የዘገየው፡ነው፤
ፀር ፡ ጠላት ፡ ወደ ፡ ኢየሩሳሌም ፡ በር፡
እንዲገባ፡አላመኑም፤

፲፫፤ ሜም፤
ምዑዝ፡እግዚአብሔር፡ማለት፡ነው፤
በኃጢአተ ፡ ነቢያቲሃ ፡ ወበጌጋየ ፡ ካህናቲሃ ፡
እለ፡ከዐዉ፡ደመ፡ጻድቃን፡በማዕከላ፤
በመካከሏ፡የጻድቃንን፡ደም፡ባፈሰሱ፡
በነቢያተ ፡ ሐሰት ፡ ኃጢአት፡ በካ
ህናተ ፡ ጣዖት ፡ በደል ፤ ፀር ፡ ጠላት ፡
ወደ፡ ኢየሩሳሌም ፡ በር፡ እንዲገባ ፡
አላመኑም፤

፲፬፤ ኖን፤
ኖላዊ፡ትጉህ፡እግዚአብሔር፡ማለት፡
ነው፤
ተሐውኩ፡ዕውራኒሃ፡በአፍአ፤
የኢየሩሳሌም ፡ ዕውራን ፡ ልቡናዎቿ ፡
እስራኤል ፡ ከኢየሩሳሌም ፡ በአፍአ ፡
በባቢሎን፡ተወ[illegible]



ወተቀብዓ ፡ አልባሲሆሙ ፡ በደም ፡ ሶበ ፡
ተጽዕሩ፤
ተወግተው ፡ በተጨነቁ ፡ ጊዜ ፡
ልብሳቸው፡በደም፡ተቀባ፤

፲፭፤ ሳምኬት፤
ሰፋኒ፡እግዚአብሔር፡ማለት፡ነው፤
ርኂቀ፡ረኀቁ፡እምርኵሳን፤
ከባቢሎን ፡ ሰዎች ፡ ፈጽማችሁ ፡ ራቁ፡
በሏቸው ፤ አንድም ፡ እምርኵሳ ፡ ቢል ፡
ከኃጢአቷ ፡ ፈጽማችሁ ፡ ራቁ ፡
በሏቸው፤
ወስብኩ፡ሎሙ፤
ንገሯቸው፤
ወበልዎሙ፡ረኀቁ፤
ራቁ፡በሏቸው፤
ወኢትግሥሡ፤
አሕዛብን፡በግብር፡አትምሰሏቸው፤
እስመ፡ተሐውኩ፤
ተሸብረዋልና፤
ወበልዎሙ ፡ ለአሕዛብ ፡ ኢይድግሙ ፡
ነቢሮታ፤
አሕዛብ ፡ በባቢሎን ፡ አይኖሩባትም ፡
ይጠፋሉ ፤ አንድም ፡ እስራኤል ፡
በባቢሎንአይኖሩባትም፡ይወጣሉ፤

፲፮፤ ዔ፤
ዓቢይ፡እግዚአብሔር፡ማለት፡ነው፤
ገጹ፡ለእግዚአብሔር፡መክፈልቶሙ፤
የእግዚአብሔር፡ገጸ፡መዓቱ፡ለእስራ፡
ኤል፡ዕድል፡ፈንታቸው፡ነው፤
ወኢይደግም፡ነጽሮቶሙ፤
በዓይነ፡ምሕረት፡አያያቸውም፤
እስመ፡ኢኀፈሩ፡ገጸ፡ካህናት፤
ሳታናብብ ፡ ካህናቱ ፡ ገጸ ፡ እግዚአብ
ሔርን፡አላከበሩምና፤
ወኢመሀሩ፡ሊቃውንተ፤
አለቆችም ፡ ለገጸ ፡ እግዚአብሔር ፡ አላ
ዘኑምና ፤ አንድም ፡ ገጹ ፡ ለእግዚአ
ብሔር ፡ የእግዚአብሔር ፡ ገጸ ፡ መዓቱ ፡
ለአሕዛብ፡ዕድል፡ፈንታቸው፡ነው፤
ወኢይደግም ፤ በዓይነ ፡ ምሕረት ፡ አያያ
ቸውም ፤ እስመ ፡ ኢኀፍሩ ፡ አናብብ ፤ የካ
ህናትን ፡ ፊት ፡ አላከበሩምና ፡
ወኢመሀሩ ፡ ሊቃውንት ፡ ለሊቃ
ውንቱ፡አላዘኑምና፤

፲፯፤ ፌ፤
ፍቁር፡እግዚአብሔር፡ማለት፡ነው፤
እንዘ፡ዓዲ፡ሕያዋን፡ንሕነ፤
እኛ፡በሕይወተ፡ሥጋ፡ሳለን፤
ጠፍአ፡አዕይንቲነ፤
ዓይናችን፡ጠፋ፤
በእንተ፡ከንቱ፡ረድኤትነ፡እንዘ፡ንሴፎ፤
ጣኦትን፡ተስፋ፡ስናደርግ፡በሕይወት፡
ሳለን፡ዓይናችን፡ጠፋ፤

፲፰፤ ጻዴ፤
ጻድቅ፡እግዚአብሔር፡ማለት፡ነው፤
ከላዕነ፡ደቂቀነ፡አይፃኡ፡መርኅበነ፤
ወደ ፡ አደባባይ ፡ እንዳይወጡ ፡ ልጆቻ
ችንን፡ከለከልን፤
ሶበ፡ቀርበ፡ጊዜነ፤
የምንጠፋበት፡ቀን፡በቀረበ፡ጊዜ፤
ወኀልቀ፡መዋዕሊነ፤
መዋዕለ ፡ ተድላችን ፡ ደስታችን ፡ በተ
ፈጸመ፡ጊዜ፤
እስመ፡በጽሐ፡ጊዜነ፤
የምንጠፋበት ፡ ጊዜው ፡ ደርሶዋልና ፡
ከላዕነ፤

www.ethiopianorthodox.org

ደቂቀነ ፡ ልጆቻችን ፡ ወደ ፡ አደባባይ ፡ እንዳይወጡ ፡ ከለከሉን ፤ አንድም ፡ ቀርበ፡ጊዜነ፡ተድላ፡ደስታ፡የምናደር ግበት ፡ ጊዜ ፡ ደረሰ ፤ ወኀልቀ ፤ መከራችን፡ተፈጸመ፡እስመ፡በጽሐ፡ ተድላ ፡ ደስታ ፡ የምናደርግበት፡ ጊዜው፡ደርሶዋልና፤

፲፱፤ ቆፍ፡
ቅሩብ፡እግዚአብሔር፡ማለት፡ነው፤

ረዋጽያነ፡ኮኑ፡እለ፡ዴገኑነ፡እምአንሥርተ፡
ሰማይ፡ላዕለ፡አድባር፤
ረዋጽያነ ፡ ኮኑ ፡ እለ ፡ ዴገኑነ ፡ ላዕለ ፤ አድባር ፡ ብሎ ፡ መግጠም ፡ ነው ፤ በተራራ ፡ የተከተሉን ፡ ጠላቶቻችን ፡ ከሰማይ፡አሞራ፡ይልቅ፡ይፈጥናሉ፤

ወረከቡነ፡እስመ፡በገዳም፡ጸንሑነ፡
ከምድረ፡በዳ፡ጠብቀውናልና፡አገኙን፤

፳፤ ሬስ፡
ርኡስ፡እግዚአብሔር፡ማለት፡ነው፤

መንፈሰ፡ገጽነ፡መሲሑ፡ለእግዚአብሔር፡
በሥልጣኑ ፡ ሰውነታችን ፡ ተጠብ ቆበት፡ይኖራል፡ብለነው፡የነበረ፡እግ ዚአብሔር ፡ ቀብቶ ፡ ያነገሠው ፡ ንጉሡ፤

ተንሥአ ፡ በመሥገርቶሙ ፡ ዝኩ ፡ ዘንቤ ፡ በጽላሎቱ፡ነሐዩ፡በውስተ፡አሕዛብ፡
በሥልጣኑ ፡ ከአሕዛብ ፡ ተጠብቀን ፡ እንኖርበታለን ፡ ብለነው ፡ የነበረ ፤ ኢኮንያን፡ሴዴቅያስ፡ተንሥአ፡በመ ሥገርቶሙ ፤ በአሕዛብ ፡ ጦር ፡ ተማ ረከ ፡ ጠፋ ፤ አንድም ፡ ሰውነታችን፡ በሥልጣኑ፡ተጠብቆ፡የሚኖር፡እግዚ አብሔር፡አብ፡ያዋሐደው፡ክርስቶስ፡ በጽላሎቱ ፡ ነሐዩ ፤ በሥልጣኑ ፡ ከአጋ ንንት፡ከመናፍቃን፡ተጠብቀን፡የምን ኖርበት፡ክርስቶስ፡በአይሁድ፡ምክር፡ ተያዘ፤

፳፩፤ ሳን፡
ሰቡሕ፡እግዚአብሔር፡ማለት፡ነው፤

ተፈሥሒ፡ወተኃሠዪ፡ወለተ፡ኤዶምያስ፤
ፍና ፡ ተሣልቆ ፡ ነው ፤ የኤዶምያስ ፡ ልጅ፡ፈጽሞ፡ደስ፡ይበልሽ፤

እንተ፡ትነብሪ፡ውስተ፡ምድረ፡ዖፅ፤
ዖስ ፡ ዖፅ፡ ይላል ፤ በኤዶምያስ ፡ የም ትኖሪ፡

እስመ ፡ ላዕሌኪ ፡ ተኃልፍ ፡ ጽዋዕ ፡ ዘእግዚአ ብሔር፡
የእግዚአብሔር ፡ ጽዋ ፡ መዓቱ ፡ በአንቺ፡ ላይ ፡ ተቃጥታለችና ፡ ወት ሰክሪ፡ማንሻ፤አንድም፡በአንቺ፡ላይ፡ ተቃጥታለችና፤

ወትሰክሪ፡
በመከራው፡አረቂ፡ትሰክሪያለሽ፤

ወትትዓረቂ፡
ከገንዘብሽ ፡ ትለዩያለሽ ፡ ማለት ፡ ባዶሽን፡ትቀሪያለሽ፤

፳፪፤ ታው፡
ትጉህ፡እግዚአብሔር፡ማለት፡ነው፤

ኀልቀ፡ኃጢአትኪ፡ወለተ፡ጽዮን፡
የጽዮን፡ልጅ፡ኃጢአትሽ፡ተፈጸመ፤

ኢይደግም፡እንከ፡አፍልሶተኪ፡
ዳግመኛ፡አላስማርክሽም፤

ይቀህዮ፡ለኃጢአትኪ፡ወለተ፡ኤዶምያስ፤
የኤዶምያስ፡ልጅ፡ኃጢአትሽን፡ይጐ በኘዋል ፡ ማለት ፡ በኃጢአትሽ ፡ ምክንያት፡መከራን፡ያመጣብሻል፤

ከሠተ፡ላዕለ፡ኃጢአትኪ፡
ኃጢአትሽን ፡ ገለጠ ፡ ማለት ፡ በኃጢ አትሽ፡መከራን፡አመጣ።



## ምዕራፍ ፡ ፭ ፤

፩፤ ተዘከር፡እግዚኦ፡ምንተ፡ኮነ፡ለነ፡
አቤቱ ፡ ለኛ ፡ የተደረገልን ፡ ተድላ ፡ ደስታ፡ምን፡እንደሆነ፡አስብ፤

ነጽር፡ወርኢ፡እግዚኦ፡ኃሣረነ፡
አቤቱ ፡ ተዋርዶአችንን ፡ እይ ፡ ተመ ልከት፤

፪፤ ዘኮነ፡ለባዕድ፡ርስትነ፡
ርስታችን፡ለባዕድ፡የሆነበትን፤

ወአብያቲነ፡ለነኪራን፡
ቤታችንም ፡ ለአሕዛብ ፡ የተሰጠበትን ተዋርዶዋችንን፡እይ፡ተመልከት፤

፫፤ ዕጓለ፡ማውታ፡ኮነ፡
እናት ፡ አባቱ ፡ ጥለውት ፡ እንደሞቱ ፡ ልጅ፡ሆነ፤

አልብነ፡አብ፡
አባት፡የለንም፤

እማቲነ፡ኮና፡ከመ፡መበለታት፡
እናቶቻችን ፡ ልጆቻቸው ፡ ሙተው ፡ እንደ፡ድኖች፡ሆኑ፤

፬፤ ወማያቲነ፡በብሩር፡ሰተይነ፡
ውኃችንን፡በብር፡ገዝተን፡ጠጣን፤

ዕፀዊነ፡በሤጥ፡ይመጽእ፡ላዕለ፡ክሳውዲነ፡
ዕንጨታችንን ፡ ዋጋ ፡ ሰጥተን ፡ ገዝ ተን ፡ በትክሻችን ፡ ተሸክመን ፡ እንመ ጣለን ፡ ይላሉ ፤ መኳንንቱ ፡ በዬዋዌ፡ ከተዋረዱ፡በኋላ፡ነው፤

፭፤ ዴገኑነ፡ፀርነ፡
አሕዛብ፡ተከተሉን፤

ሠራሕነ፡
በመከራ፡ደከምን፤

ወኢያዕረፉነ፡
ከመከራው፡አላሳረፉንም፤

፮፤ ግብፅ፡ወሀቡነ፡እደ፡
ግብፃውያን ፡ ላያድኑንን ፡ እንረዳች ኋለን፡አሉን፤

አሦር፡በልዐነ፡ለጸጊብ፡
ስልምናሦር ፡ ገንዘባችንን ፡ ተካፍሎ ፡ በላብን ፤ አንድም ፡ ግብፅ ፤ ወሀቡነ ፡ እደ፡ወኢያጽገቡነ፡ይላል፤
ግብፃውያን ፡ እጅ ፡ ታህል ፡ እንጀራ ፡ ሰጡን ፤ አላጠገቡንም ፡ ይላሉ ፡ እስራኤል፤

፯፤ አበሱ፡ለሊሆሙ፡
አሕዛብ፡በደሉ፤

ንሕነ፡ኃጢአቶሙ፡ፆርነ፡
እኛም ፡ በኃጢአታቸው ፡ የመጣውን ፡ ፍዳ፡ተቀበልን፡ይላሉ፡እስራኤል፤

፰፤ አግብርት፡ተሰልጡ፡ላዕሌነ፡
ባሮች፡በእኛ፡ላይ፡ሰለጠኑብን፤

ወአልቦ፡ዘያድኅነ፡እምኔሆሙ፡
ከነዚያ፡የሚያድን፡የለም፤

፱፤ በነፍስነ፡ናመጽእ፡ሲሳየነ፡
በሰውነታችን ፡ ተገዝተን ፡ የዕለት ፡ ምግባችንን፡እንመገባለን፤

እምገጸ፡ኲናተ፡ገዳም፡ተሐውከ፡
በምድረ፤ በዳ ፡ ካለው ፡ ጦር ፡ የተነሣ ፡ ታወከ፡ተሸበረ፤

፲፤ እምገጸ፡ረኃብ፡ተጸማኅየዩ፡
ከገጸ ፡ መዓቱ ፡ የተነሣ ፡ በረኃብ ፡ ጠወለጉ፤

www.ethiopianorthodox.org

፲፩፤ አንስት፡በጽዮን፡ኃሥራ፡
ሴቶች፡በጽዮን፡ጐሰቈሉ፤
ወደናግል፡በአህጉረ፡ይሁዳ፡
ቈነጃጅቱም ፡ በይሁዳ ፡ አውራጃ ፡ ጐሰቈሉ፤

፲፪፤ መላእክት፡በእደዊሆሙ፡ተሰቅሉ፡
አለቆች ፡ በእጃቸው ፡ በሥሩት ፡ ሥራ ፡ በፍዳ፡ተያዙ፤
ገጸ፡ሊቃውንት፡ኢያክበሩ፡
የሊቃውንቱን፡ፊት፡አላከበሩም፤

፲፫፤ ወራዙት፡ማሕረፀ፡ፆሩ፡
ጐልማሶች፡ወፍጮውን፡ተሸከሙ፤
ወመሐዛት፡በዕፀው፡ደክሙ፡
ጐልማሶች ፡ ሕፃናቱ ፡ እንጨት ፡ በመሸከም፡ደከሙ፤

፲፬፤ ሊቃውንት ፡ እምነ ፡ አንቀጽ ፡ ተሥእሩ፡
አለቆች ፡ ከአደባባይ ፡ ተሻሩ ፤ ሽማግ ሌዎች፡ከአደባባይ፡ታጡ፡ብትልም፡ ይሆናል፤
ወለወራዙት፡ማኅሌቶሙ፡ተሥዐረ፡
የጐልማሶች፡ዘፈናቸው፡ተድላቸው፡ ደስታቸው፡ጠፋ፤

፲፭፤ ፍሥሐ፡ልብነ፡ተመይጠ፡ለላሀ፡
ፍሥሐ፡ልብነ፡ማኅሌትነ፡ሲል፡ነው፤ ደስ፡ብሎን፡የምንዘፍነው፡ዘፈናችን፡ ወደ፡ልቅሶ፡ተመለሰ፤

፲፮፤ ወድቀት፡አክሊለ፡ርእስነ፡
የራሳችን ፡ ክብር ፤ አንድም ፡ የኢየሩ ሳሌም ፡ ክብር ፡ ጠፋች ፤ አንድም ፡ የራሳችን ፡ ክብር ፡ የሚሆን ፡ ንጉሡ ፡ ተዋረደ፤
ወይኬ፡ለነ፡እስመ፡ጌገይነ፡
በድለናልና፡ወዮልን፤

፲፯፤ በእንተ፡ዝንቱ፡ደወየ፡ልብነ፡
ስለዚህ፡ነገር፡ልቡናችን፡አዘነ፤
በእንተ ፡ እሉ ፡ ጸልመ ፡ ዓይንነ ፡ በእንተ ፡ ደብረ፡ጽዮን፡
ስለ ፡ ደብረ ፡ ጽዮን ፡ ስለ ፡ ልጆቻችን ፡ መሞት፡ስናለቅስ፡ዓይናችን፡ጠፋ፤

፲፰፤ እስመ፡ኮነ፡ገዳመ፡
ከተድላ፡ከደስታ፡ከረድኤት፡ምድረ፡ በዳ፡ሆነናልና፤
ቈናጽል፡ሖሩ፡ቦቱ፡
አሕዛብ፡ሠልጥነው፡ኖሩበት፤

፲፱፤ አንተሰ፡እግዚኦ፡ለዓለም፡ትነብር፡
አቤቱ ፡ አንተ ፡ ግን ፡ እንደ ፡ ኢየሩሳ ሌም፡አትጠፋም፤ለዘላለም፡ፀንተህ፡ ትኖራለህ፤
ወመንበርከሂ፡ለትውልደ፡ትውልድ፡
ዙፋንህም ፡ ለልጅ ፡ ልጅ ፡ ዘመን ፡ ጸንቶ፡ይኖራል፤

፳፤ ለምንት፡ለግሙራ፡ትረሥአነ፡
ለምን፡ፈጽመህ፡ትዘነጋናለህ፤
ወተኀድገነ፡ለነዋህ፡መዋዕል፡
ነዋሃ ፡ መዋዕለ ፡ ሲል ፡ ነው ፤ ብዙ ፡ ዘመን፡በረድኤት፡ለምን፡ትለየናለህ፤

፳፩፤ ሚጠነ፡እግዚአብሔር፡ኀቤከ፡
እግዚአብሔር ፡ በአምልኮት ፡ ወደ ፡ አንተ፡መልሰን፤
ወንትመየጥ፡
እኛም ፡ በንስሐ ፡ ወደ ፡ አንተ ፡ እንመለስ፤
ሐድስ፡መዋዕሊነ፡ከመ፡ትካት፡
እንደቀደመው፡ዘመናችን፡አጽና፤

፳፪፤ ለእመ፡መንኖ፡መነንከነ፡
ፈጽመህ፡ብትንቀን፡ግን፤
ተማዕከ፡ላዕሌነ፡ጥቀ፡
በእኛ፡ላይ፡እጅግ፡ተበሳጨህ፤



# አርእያ፡መጽሐፍ፡ ዘኤርምያስ፤

## ጉባዔ፤

አርአያ፡መጽሐፍ፡ዘኤርምያስ፡ዘፈነወ፡ኀበ፡ እለ ፡ ፄወዎሙ ፡ ንጉሠ ፡ ባቢሎን ፡ ሀገረ ፡ ባቢሎን፡
የባቢሎን፡ንጉሥ፡ማርኮ፡በባቢሎን፡ ወደ ፡ አኖራቸው ፡ ሕዝብ ፡ የላከው፡ ኤርምያስ ፡ የተናገረው ፡ ነገር ፡ ይህ ፡ ነው ፤ ወርኢኩ ፡ አርአያ ፡ ባሕቲትየ ፡ እንዲል ፡ አንድም ፡ ፊት ፡ የጻፈውን ፡ መጽሐፍ ፡ የሚመስል ፡ መጽሐፍ ፡ ይህ፡ነው፤አንድም፡መልክዓ፡ጣኦት፡ ዘያርኢ ፡ ቦቱ ፤ ይላል ፡ የጣኦቱን ፡ መልክ ፡ ለይቶ ፡ ለይቶ፡ የሚያሳይ ፡ መጽሐፍ፡ይህ፡ነው፤
ይንግርዎሙ፡ዘአዘዘ፡እግዚአብሔር፡
ነቢያት ፡ ካህናት ፡ እግዚአብሔር ፡ ያዘዘውን፡ነገር፡ለእስራኤል፡ይነግሩ ዋቸው፡ዘንድ።

## ምዕራፍ፡፩፤

፩፤ በእንተ፡ኃጢአትክሙ፡ዘአበስክሙ፡ ለእግዚአብሔር ፡ ወሰዱክሙ ፡ ባቢሎን ፡ ትንበሩ፡ ህየ፡ብዙኃ፡መዋዕለ፡እስከ፡ሳብዕ፡ ትውልድ፡
እግዚአብሔርን ፡ በበደላችሁበት ፡ ኃጢአታችሁ ፡ እስከ ፡ ሰባት ፡ ትውልድ፡ ድረስ፡በባቢሎን፡ትኖሩ፡ ዘንድ ፡ ወደ ፡ ባቢሎን ፡ ወሰዷችሁ ፡ ሳብዕ ፡ ያለው ፡ የተማረኩ ፡ በሕዝ ቅያስ፡መንግሥት፡ነው፤
ምናሴ፡
አሞጽ፡
ኢዮስያስ፡
ኢኮንያን፡
ኤልያቄም፡
ሰላትያል፡
ዘሩባቤል፡
በሰባተኛው ፡ በዘሩባቤል ፡ ወጥተ ዋልና፤አንድም፡የተገዙበትን፡ሰባት፡ አድርግ ፡ የተማረኩ ፡ በሕዝቅያስ ፡ መንግሥት፡ነው፤
ሕዝቅያስ፡
ምናሴ፡
አሞጽ ፡ ብለህ ፡ በስምንተኛው ፡ በዘሩ ባቤል፡ወጥተዋል፤

፪፤ ወእምዝ ፡ አወጽአክሙ ፡ በሰላም ፡
ከዚህ ፡ በኋላ ፡ በፍቅር ፡ በደስታ ፡ ከባቢሎን፡አወጣችኋለሁ፤
ወይእዜሰ፡ትሬእዩ፡አማልክተ፡ባቢሎን፡
ዛሬ ፡ ግን ፡ የባቢሎንን ፡ ጣኦታት ፡ ታያላችሁ፤
አማልክተ፡ዘወርቅ፡ወዘብሩር፡
የወርቅ ፡ የብር ፡ የሚሆኑ ፡ ጣኦታትን ፡ ታያላችሁ፤
ወዘዕፅ፡
የእንጨት፡የሚሆኑ፤
ይፀውርዎሙ፡በመታክፍቲሆሙ፤
በትክሻቸው፡ተሸክመው ፡ይዘዋቸው፡ ይሔዳሉ፤
ወይጌርምዎሙ፡አሕዛብ፡
አሕዛብ፡ያስፈሯቸዋል፤

፫፤ ዑቁ፡እንከ፡ኢትኩኑ፡ከማሆሙ፡
እንደነሱ፡እንዳትሆኑ፡ዕወቁ፤

፬፤ እመ ፡ ርኢክሙ ፡ አሕዛበ ፡ በቅድ ሚሆሙ፡ወበድኅሬሆሙ፡ይሰግዱ፡ሎሙ፤

www.ethiopianorthodox.org

አሕዛብን ፡ በፊታቸው ፡ በኋላቸው ፡
ሁነው፡ለጣኦታቱ፡ሲሰግዱ፡ብታዩ፤

በሉ፡በልብክሙ፤
በልቡናችሁ፡እንዲህ፡በሉ፤

ለከ፡ርቱዕ፡ይስግዱ፡እግዚኦ፤
አቤቱ ፡ አገባብስ ፡ ለአንተ ፡ ሊሰግዱ ፡
ይገባል፡በሉ፤

፭፤እመ፡በሙ፡ልሳን፡ዘገብሮ፡ፀራቢ፤
ለጣኦታቱ፡አንደበት፡እንዲኖራቸው፡
እንጨት፡ጠራቢ፡የሠራው፡ነው፤

ወውእቱ፡ዘወርቅ፡ወዘብሩር፤
ይኸውም፡የወርቅ፡የብር፡ነው፤

ሐሠት፡እሙንቱ፤
ጣዖታቱ፡ሐሰት፡ናቸው፤

ወኢይክሉ፡ተናግሮ፤
መናገር፡አይቻላቸውም፤

፮፤ ወከመ ፡ ድንግል ፡ እንተ ፡ ሥርጉት ፡
በወርቅ፤
በወርቅ ፡ እንደ ፡ አጌጠች ፡ እንደ ፡
ድንግል፤

፯፤ ገብሩ ፡ ሎሙ ፡ ቀጸላ ፡ ዘወርቅ ፡
ወዘብሩር፤
የወርቅ፡የብር፡የሚሆን፡ቀጸላ፡አደረ
ጉላቸው፤

፰፤ ወያለብስዎሙ፡ከመ፡ሰብእ፤
እንደ፡ሰው፡ልብስ፡ያለብስዋቸዋል፤

፱፤ ወለርእሶሙ ፡ ኢየኃድጉ ፡ ዛኅሎሙ ፡
ልብስም ፡ ቢያለብሷቸው ፡ ጣዖታቱ ፤
ዝገታቸውን ፡ አይተዉም ፤ አንድም ፡
ኢየኃጉሉ ፡ ዘኃየሎሙ ፡ ይላል ፤ ቢል ፡
የተበረታታባቸውን፡አያጠፉም፤

፲፤ ወይከድንዎሙ፡በሜላት፤
ነጭ፡ሐር፡ያለብሷቸዋል፤

ወይመዘምዝዎሙ፡እምፀበለ፡ቤት፤
በቤት፡ካለው፡ሸቱ፡ይቀቧቸዋል፤

፲፩፤ ወያእኀዝዎሙ፡በትረ፡ከመ፡ሰብእ፤
የእኔ፡ጣኦት፡ሥልጣን፡ገንዘቡ፡ነው፡
ሲል፡እንደ፡ሰው፡ብትር፡ያሲዘዋል፤

ወለዘገፍዖሙሂ፡ኢይትቤቀልዎ፤
የበደላቸውንም፡ሰው፡ተበቅለው፡አያ
ጠፉትም፤

፲፪፤ ወቦ፡ውስተ፡እዴሁ፡ጉድብ፤
የኔ ፡ ጣዖት ፡ ሥልጣን ፡ አለው ፤ ጽኑ ፡
ነው ፤ የበደሉትን ፡ ተበቅሎ ፡ ያጠፋል ፡
ሲል፡ገጀሞ፡የሚያሲዘው፡አለ፤

ወርእሶ፡ኢያድኅን፡እምሰረቅት፤
ራሱን ፡ ከሌባ ፡ አያድንም ፤ አንድም ፡
እምስርቀት፡ቢል፡ራሱን፡ከመሰረቅ፡
አያድንም፤

ወበዝንቱ ፡ ይትዓወቁ ፡ ከመ ፡ ኢኮኑ ፡
አማልክተ፤
አማልክት ፡ እንዳይደሉ ፡ በዚህ ፡
ይታወቃሉ፤

ኢትፍርህዎሙ፡እንከ፤
እንግዲህ፡ወዲህ፡አትፍሯቸው፤

፲፫፤ ከመ፡ንዋይ፡ዘይትቀጠቀጡ፡ወኢይ
በቍዑ፤
የዘይት ፡ ዕቃ ፡ እንዳይረባ ፡ እንዳይ
ጠቅም ፤ አንድም ፡ ከመ ፡ ንዋይ ፡ ዘይት
ቀጠቀጥ ፡ ወኢይበቍዕ ፡ ብርሌ ፡
ብርጭቆ ፡ ከተሠበረ ፡ በኋላ ፡ እንዳ
ይረባ፡እንዳይጠቅም፤

ከማሁ፡አማልክቲሆሙ፤
ጣኦቶቻቸውም ፡ አይረቡም ፡ አይጠ
ቅሙም፤



፲፬፤ ወይቄንውዎሙ፡ውስተ፡ቤት፤
በቤት፡አስጠግተው፡ያቆሙዋቸዋል፤

ወይመልዕ፡ውስተ፡አዕይንቲሆሙ፡ፀበል፡
እምግብረ፡ሰብእ፡ዘይበውዕ፤
ከሚወጣው ፡ ከሚገባው ፡ ከሰው ፡
ሥራ፡ የተነሣ ፡ በፊታቸው ፡ ትቢያ ፡
ይመላል፤

፲፭፤ ወየአጽውዎሙ፡ገነውቶሙ፡ከመ፡
ኢይስርቅዎሙ፤
እንዳይሰርቋቸው ፡ ካህናተ ፡ ጣዖቱ ፡
ቤት፡ይዘጉባቸዋል፤

፲፮፤ መኅትወ፡ያኃትዉ፡ሎሙ፤
መብራት፡ያበሩላቸዋል፤

ወአልቦ፡ዘይሬእዩ፤
የሚያዩት፡የለም፤

፲፯፤ ወእመሂ፡ሐድዎሙ፡አልባሲሆሙ፡
ኢየአምሩ፤
ልብሳቸውን፡ቢገፍፏቸው፡አያውቁም፤

፲፰፤ ወይጸልም ፡ ገጾሙ ፡ እምጢስ ፡
ዘይጠይስ፡ውስተ፡ቤት፤
በቤት ፡ ውስጥ ፡ ከሚጤሰው ፡ ጢስ ፡
የተነሣ፡ፊታቸው፡ይጠቍራል፤

፲፱፤ ወይነብሩ ፡ ውስተ ፡ አርዕስቲሆሙ ፡
ፅግነት፤
ፅግነት፡የሌሊት፡ዖፍ፤

ወአዕዋፍ፤
ጉጉት፤

ወድመት፤
ድመት፡በቁሙ፤
በራሳቸው፡ላይ፡ይቀመጣሉ፤

፳፤ ወበዝንቱ ፡ ተአምሩ ፡ ከመ ፡ ኢኮኑ ፡
አማልክተ፤
አማልክት፡እንዳይደሉ፡በዚህ፡ታው
ቋቸዋላችሁ፤

ኢትፍርህዎሙ፡እንከ፤
እንግዲህ፡ወዲህ፡አትፍሯቸው፤

፳፩፤ ከመ፡ወርቅ፡እመ፡አንበርዎ፤
ወርቅ፡ካኖሩት፡በኋላ፡ወዲያ፡ወዲህ፡
እንዳይል፤

ወኢኀብረትዎ፡ኢይበርህ፤
ካልወለወሉት፡እንዳያበራ፤

ወሶበሂ፡ይሰበኩ፡ኢየአምሩ፤
እነዚህም ፡ ተመትተው ፡ በተሠሩ ፡
ጊዜ፡አያውቁም፤

፳፪፤ ወአልቦሙ፡መንፈስ፤
ዕውቀት፡የላቸውም፤

፳፫፤ ወይፀውርዎሙ ፡ ዲበ ፡ መትከፍት ፡
ከመ፡ይትዓወቅ፡ኀሣሮሙ፤
ተዋርዶዋቸው፡ይገለጥ፡ዘንድ፡በትከ
ሻቸው ፡ ተሸክመው ፡ ይዘዋቸው ፡
ይሔዳሉ፤

፳፬፤ ወእመሂ፡ወድቁ፡ውስተ፡ምድር፤
ከምድርም፡ቢወድቁ፤

ኢይትነሥኡ፡ለሊሆሙ፤
ራሳቸው፡አይነሡም፤

ወእመሂ፡አንሥእዎሙ፤
ቢያነሡዋቸውም፤

ኢይቀውሙ፡ለሊሆሙ፤
እነርሱ፡አይቆሙም፤

ከመ ፡ ምውት ፡ ያቀርቡ ፡ መብልዓ ፡ ወመሥ
ዋዕተ፤
እንደ ፡ ሞተ ፡ ምግቡን ፡ መሥዋዕቱን ፡
ያቀርቡላቸዋል፤

፳፭፤ ወይበልዕዎሙ፡ገነውቶሙ፤
ካህናተ ፡ ጣዖቱ ፡ ይበሉታል ፤ ይበሉባ
ቸዋል፤ብትልም፤

www.ethiopianorthodox.org

፭፮፤ በዝኩ ፡ አዕምሩ ፡ ከመ ፡ ኢኮኑ ፡ አማልክተ፤
አማልክት ፡ እንዳይደሉ ፡ በዚህ ፡ ዕወቁ፤

ወኢትፍርህዎሙ፤
አትፍሯቸው፤

፭፯፤ ዕፀው፡ወዕብን፡እሙንቱ፤
እነዚህ፡ጣዖታቱ፡እንጨት፡ደንጊያ፡ናቸው፤

ወእመኒ፡አውየዉ፡ሎሙ፡ኢይሰምዑ፤
ቢጮሁላቸውም፡አይሰሙም፤

፭፰፤ ኢይክሉ ፡ ገቢረ ፡ ወኢዘአህሰመ ፡ ሎሙ፤
ሥራ፡መሥራት፡አይችሉም፤

ወኢአሠንዮ፤
ወዳጃቸውን፡መጥቀም፤

ወኢአእከዮ፤
ጠላታቸውን ፡ መጉዳት ፡ አይቻላቸውም፤

ኢያነግሡ፤
እግዚአብሔር፡ቢሽር፡ጣዖታቱ፡አያነግሡም ፡ (ማንገሥ ፡ አይቻላቸውም) ብትልም፤

ወኢይሥእሩ፤
እግዚአብሔር ፡ ቢያነግሥ ፡ አይሽሩም ፤ መሻር ፡ አይቻላቸውም ፡ ብትልም፤

፭፱፤ ኢያብዕሉ፤
ቢነሳ፡አያከብሩም፤

ወኢያነድዩ፤
ቢሰጥ፡አይነሡም፤

፷፤ ኢይቀትሉ፤
ቢያድን፡አይገድሉም፤መግደል፡አይቻላቸውም፡ብትልም፤

ወኢያሐይዉ፤
ቢገድል፡አያድኑም፤

ወኢያድኅንዎ ፡ ለድኩም ፡ እምእደ ፡ ዘይትዔገሎ፤
ድኃውን፡ከሚቀማው፡ሰው፡እጅ፡አያድኑትም፤

፷፩፤ ወእመኒ፡መጽኦሙ፡ፀባኢት፡
አርበኛም፡ቢመጣባቸው፤

የሐሥሡ ፡ ገነውቶሙ ፡ ኅበ ፡ ይትኃብኡ ፡ ምስሌሆሙ፤
ከነሱ፡ጋራ፡የሚሠወሩበት፡ጣዖቱን፡ይሻሉ ፤ አንድም ፡ ኅበ ፡ የኅብኡ ፡ ምስሎሙ፡ጣዖታቸውን፡የሚሠውሩ በትን፡ቦታ፡ይሻሉ፤

፷፪፤ እፎ፡እንከ፡አማልክት፡ዘርእሶሙ፡ኢያድኅኑ፤
ራሳቸውን ፡ ማዳን ፡ የማይቻላቸው ፡ እነዚህ ፡ እንዴት ፡ አማልክት ፡ ይባላሉ፤

፷፫፤ ወይትዐወቁ ፡ ከመ ፡ ግብረ ፡ እደ፡ ዕጓለ፡እመሕያው፡እሙንቱ፤
እነዚህ፡ጣዖታቱ፡የሰው፡እጅ፡ሥራ፡እንደ፡ሆኑ፡ይታወቃሉ፤

ወአልቦሙ፡ግብረ፡አምላክ፤
የአምላክነት፡ሥራ፡የላቸውም፤

ኢያዘንሙ፤
ዝናም ፡ መዝነሙን ፡ ቢተው ፡ አያዘንሙም፤ማዝነምም፡አይቻላቸውም፡ብትልም፤

ወኢያኃድጉ፤
ዝናሙ ፡ በዝቶ ፡ ቢዘንም ፡ ዝናሙን፡ ማስቀረት፡አይቻላቸውም፤

ከመ፡ቋዓት፡ማዕከለ፡ሰማይ፡ወምድር፤
በሰማይና ፡ በምድር ፡ መካከል ፡ እንደሚኖሩ፡እንደ፡ቋዓት፡(ቁራ) ናቸው፤ እሊህ፡ቋዓት፡ከሰማይም፡ሳይደርሱ፡



ከጠፈርም ፡ ከምድርም ፡ ሳይደርሱ ፡ በመካከል ፡ ይሔዳሉ፤ እነዚህም ፡ ጣዖታቱ፡አማልክት፡እንዳይሏቸው፡ፍጡራን ፡ ናቸው፤ ፍጡራን ፡ እንዳይሏቸው ፡ አማልክት ፡ ናቸውና ፡ ይባላሉና፡ብትልም፤

፷፬፤ ወእመኒ፡ውዕየ፡ቤተ፡አማልክት፤
የጣዖታቱም፡ቤት፡ቢቃጠል፤

ነገውቶሙ፡ይጐይዩ፤
ካህናተ፡ጣዖቱ፡ይሸሻሉ፤

ወያድኅኑ፡ነፍሶሙ፤
ሸሽተው ፡ ሰውነታቸውን ፡ ከጥፋት ፡ ያድናሉ፤

እሙንቱሰ፡ከመ፡ሠርዌ፡ይውዕዩ፡በማዕከል፤
እነሱ፡እንደምሰሶ፡በመካከል፡ይቃጠላሉ፤

፷፭፤ ወእፎ፡እንከ፡አማልክት፡እሙንቱ፡ዘኢይትቤቀሉ፤
ጠላታቸውን፡ተበቅለው፡የማያጠፉ፡እነዚህ ፡ እንደምን ፡ አማልክት ፡ ይባላሉ፤

፷፮፤ ወኢያድኅኑ፡ርእሶሙ፡እምሰራቂ፤
ራሳቸውን፡ከሌባ፡አያድኑም፤እምሰርቀት፡ቢል፡ራሳቸውን፡ከመሰረቅ፡የማያድኑ ፡ እነዚህ ፡ ጣዖታቱ ፡ እንዴት፡አማልክት፡ይባላሉ፤

ሐሠዉኬ፤
እነዚህ፡ኃሠት፡ነገር፡ተናገሩ፤

፷፯፤ ወኢኮኑ፡አማልክተ፤
አማልክት፡አይደሉም፤

ማዕዖ፡ጥቀ፡ያድኅን፡ዘውስተ፡ቤት፤
መዝጊያስ ፡ እንኳ ፡ በቤት ፡ ውስጥ ፡ ያለውን፡ያድናል፤

ኢይረግሙ፤
ጠላታቸውን፡አይረግሙም፤ረግመው፡አያጠፉም፡ብትልም፤

ወኢይድኅኑ፤
ወዳጃቸውን፡መርቀው፡አይጠቅሙም፤

ወኢያሬእዩ፡ትእምርተ፡በሰማይ፤
በሰማይ፡ምልክት፡አያሳዩም፤

ወኢያበርሁ፡ከመ፡ፀሐይ፡ወወርኅ፤
በሰማይ፡ፀሐይ፡ጨረቃን፡ፈጥረው፡አያበሩም፤

፷፰፤ እንስሳ፡ይኄይሶሙ፤
ከብት፡ይበልጣቸዋል፤

፷፱፤ ወዘይክል፡ጐይየ፤
መሸሽ ፡ የሚቻለው ፡ ሁሉ ፡ ይበልጣቸዋል፤

፸፤ ከመ ፡ በድን ፡ ዘውስተ ፡ ጽልመት ፡ ይነብር፤
የዘገየ ፡ ሬሣ ፡ በጨለማ ፡ ውስጥ ፡ እንዲኖር፤

፸፩፤ ከማሁ፡አማልክቲሆሙ፤
ጣዖቶቻቸውም፡በጨለማ፡ይኖራሉ፤

፸፪፤ ይኄይስ ፡ ብእሲ ፡ ዘአልቦ ፡ ጣዖት ፡ ወርኅቀ፡እምዕዕለት፤
መምለኬ፡ጣዖት፡ተብሎ፡ከሚሰደብ፡እንጨት ፡ ጠርቦ ፤ ደንጊያ ፡ አለዝቦ ፤ ጣዖት ፡ ከሚያመልክ ፤ መምለኬ፤ ጣዖት ፡ ተብሎ ፡ የማይሰደብ ፡ እንጨት፡ ጠርቦ ፡ ደንጊያ ፡ አለዝቦ ፡ ጣዖት፡የማያመልክ፡ሰው፡ይሻላል፤ እርሱን፡ከተዉ፡እንደምን፡ሁነው፡ቢኖሩ፡ይሻል፡ኑረዋል፡ቢሉ?እንደ፡አረሚ፡ማን፡ፈጠረህ፡ሲሉት፡አባቴ፡እንዲህ፡እያለ፡ ከአዳም፡ይደርሳል፤ አዳምንስ፡ሲሉት፡ከእግዚአብሔር፡ይደርሳልና፡እንዲህ፡አለ።

www.ethiopianorthodox.org

# ትንቢት፡ዘኤርምያስ፤
## ምዕራፍ ፡ ፶ ፡

፩፤ ይቤሎ፡ኤርምያስ፡ለጸስኮር፡
ኤርምያስ፡ጳስኮርን፡እንዲህ፡አለው፤
አንትሙሰ፡ትትቃረንዋ፡ለጽድቅ፡
እናንተ፡ግን፡ጽድቅን፡ሕግን፡ሃይማኖትን፡ትቀዋወሚታላችሁ፤
ምስለ፡አበዊክሙ፤
እንደ፡አባቶቻችሁ፤
ወደቂቅክሙ ፡ እለ ፡ ይትነሥኡ ፡ እምድኅሬክሙ፤
ከእናንተ ፡ በኋላ ፡ የሚነሡ ፡ ልጆቻችሁም፡ይቀዋወሚታል፤

፪፤ ወእሙንቱሰ ፡ ገብሩ ፡ ኃጢአተ ፡ ምንንተ፤
ከአባቶቻችሁ ፡ ይልቅ ፡ ሰው ፡ ሁሉ ፡ ያልሠራት ፡ ኃጢአትን ፡ ይሠራሉ ፤ ከዚያ ፡ አስቀድሞ ፡ የሠራት ፡ ስሌለ ፡ ምንንት፡አላት፤ሰው፡ቢታበይ፡በባልንጀራው፡ነው፤እሊህ፡ግን፡ፈጣሪያቸውን፡ሸጠዋልና፤
ይሠይጥዎ፡ለዘአልቦ፡ሤጥ፡
አመጣው፤ዋጋ፡የማይተመንለት፡ክርስቶስን፡ይሸጡታል፤
ወያሐምምዎ፡ለዘኢአበሰ፡
ደዌ፡ሥጋ፡ደዌ፡ነፍስን፡የሚፈውስ፡ጌታን፡መከራ፡ያጸኑበታል፤
ወይኴንንዎ፡ለዘይሠሪ፡ኃጢአተ፡
ኃጢአትን፡የሚያሥተሠርይ፡እሱን፡ይሙት፡በቃ፡ይፈርዱበታል፤

፫፤ ወይነሥኡ ፡ ሠላሳ ፡ ብሩረ ፡ ሤጠ ፡ ለክቡር፡
የክቡር ፡ የክርስቶስን ፡ ዋጋ ፡ ይሁዳ ፡ ዘመዶቹ፡ይቀበሉታል፤አንድም፡ይነሥእዎ፡ለ፴፡ብሩር፡ይላል፤ይቀበሉበታል፤
ዘተከሀሉ፡ደቂቀ፡እስራኤል፡
ዘይሠይጥዎ ፡ ሲል ፡ ነው ፤ አይሁድ ፡ ካህናቱ ፡ የሸጡት ፤ አንድም ፡ ዘአክበርዎ ፡ ይላል ፡ ሐዋርያት ፡ ያመኑት ፡ የክቡር፡የክርስቶስን፡ዋጋ፡ይቀበላሉ፤ አንድም ፡ ሕፃናት ፡ ዘቤተ ፡ ልሔም ፡ ሆሣዕና ፡ በአርያም ፡ ቡሩክ ፡ ዘይመጽእ፡ ብለው ፡ ያመሰገኑትን ፡ አንድም፡እምደቂቀ፡እስራኤል፡ቢል፡ ከእስራኤል ፡ ልጆች ፡ ተለይተው ፡ ሥላሴ፡በማኅፀን፡ያከበሩትን፡የክርስቶስን፡ዋጋ፡ይቀበላሉ፤
ወይሁብዎ፡ለውእቱ፡ብሩር፡ውስተ፡ዐፀደ፡ለብሐዊ፡
ያንን፡ብር፡ለአንጥረኛ፡ሪም፡መግዣ፡ይሰጡታል፤

፬፤ በከመ፡አዘዘኒ፡እግዚአብሔር፡ከማሁ፡እነብብ፡
ይሁብዎ ፡ ማለትን ፡ እግዚአብሔር ፡ እንደ ፡ ገለጸልኝ ፡ እናገራለሁ ፤ አንድም፡ ይሠይጥዎ ፡ ማለትን ፡ እግዚአብሔር፡እንደ፡አዘዘኝ፡እናገራለሁ፤ ስንኳን ፡ የባሕርይ ፡ አምላክ ፡ ክርስቶስን ፡ ሩቅ ፡ ብእሲ ፡ ማለት ፡ ቀርቶ ፡ ደግን፡ሰው፡ተሸጠ፡ተለወጠ፡ማለት፡ አገባብ ፡ ሥርዓት ፡ አይደለምና፡ እግዚአብሔር፡እንደ፡አዘዘኝ፡እናገራለሁ፡ አለ፤

፭፤ ወበእንተዝ፡ይወርድ፡ላዕለ፡ርእሶሙ፡እስከ፡ለዓለም፡
ስለዚህ ፡ ነገር ፡ እስከ ፡ ዘለዓለሙ ፡ በራሳቸው፤
ወላዕለ፡ውሉዶሙ፡ድኅሬሆሙ፡ይመጽእ፡ጥፍዓት፡
ከነሱም፡በኋላ፡በልጆቻቸው፡መቻያ፡ጥፋት፡ይመጣል፤



የንጹሐ፡ባሕርይ፡የክርስቶስን፡ደም፡ አፍስሰዋልና ፡ ይኸንንም ፡ አይሁድ ፡ ዘለፋ ፡ ተግሣጽ ፡ ቢያጸናባቸው ፡ ቄንጽለው ፡ ጥለውት ፡ ነበር ፤ ኋላ ፡ ግን ፡ ሐዋርያት ፡ ከቦታው ፡ አግብተው ፡ ጽፈውታል፤
ወስብሐት፡ለእግዚአብሔር፡አሜን።

፮፤ ተረፈ፡ነገር፡ዘባሮክ፡
### ጉባዔ፤
ለባሮክ ፡ የተገለፀለት ፡ ከኤርምያስ ፡ የቀረው ፡ ያልተገለፀለት ፡ ይህ ፡ ነው ፤ ለኤርምያስ ፡ ያልተገለፀለትስ ፡ ለባሮክ፡ አልተገለፀለትም ፡ ብሎ ፡ ኤርምያስ ፡ እየነገረው ፡ ሲጽፍ ፡ ከባሮክ፡የቀረው፡ይህ፡ነው፤ኋላ፡ተገልፆለት፡የጻፈው፡ይህ፡ነው፤አንድም፡ ባሮክ፡የተናገረው፡ብዙ፡ነገሩ፡ይህ፡ነው፤
ዘኢኮነ፡ኅቡዓ፡
ተሠውሮ ፡ የሚቀር ፡ ያይደለ ፡ ተጽፏልና ፤ አንድም ፡ በሩቅ ፡ ጊዜ ፡ የሚደረግ፡ያይደለ፡በቅርብ፡ፈጥኖ፡ ነው ፡ እንጂ ፤ አንድም ፡ ሳይደረግ ፡ የሚቀር፡ያይደለ፤
ዘአመ፡ፄወዉ፡ባቢሎን፡
የባቢሎን ፡ ሰዎች ፡ እስራኤልን ፡ በማረኩ፡ጊዜ፤

፯፤ ወኮነ ፡ ሶበ ፡ ፄወዎሙ ፡ ለደቂቀ ፡ እስራኤል፡ንጉሠ፡ከላውዴዎን፡
የከላውዴዎን፡ንጉሥ፡የእስራኤልን፡ ልጆች፡በማረካቸው፡ጊዜ፡እንዲህ፡ ሆነ፡
ነበቦ፡እግዚአብሔር፡ለኤርምያስ፡
እግዚአብሔር ፡ ኤርምያስን ፤ ተናገረው፤

፰፤ ወይቤሎ፡ኤርምያስ፡ኅሩይየ፡
ወዳጄ፡ኤርምያስ፡ብሎ፡ጠራው፤
ተንሥእ፡ወፃዕ፡እምዛቲ፡ሀገር፡
ከዚህች፡ሀገር፡ተንሥተህ፡ውጣ፤
አንተ፡ወባሮክ፡
አንተና፡ባሮክ፡ውጡ፤
እስመ ፡ ሀሎኩ ፡ አማስና ፡ እምብዝኀ ፡ ኃጢአቶሙ፡ለእለ፡ይነብርዋ፡
በሚኖሩባት ፡ ሰዎች ፡ ኃጢአት ፡ አጠፋት፡ዘንድ፡አለኝና፤

፱፤ እስመ፡ጸሎትከ፡ጽኑዕ፡ከመ፡ዓምድ፡በማዕከለ፡ሀገር፡
እስከ፡አሁንም፡ድረስ፡ሳላጠፋቸው፡ መቅረቴ፡የአንተ፡ጸሎት፡በከተማ፡ መካከል፡እንደ፡ጽኑ፡ዓምድ፡ሆኖ፡እየጠበቃት፡ነው፤
ወከመ፡ቅጽር፡ዘአድማስ፡ዓውዳ፤
ዙሪያዋን፡በአድማስ፡እንዳለ፡ቅጽር፡ ነው፡ጠፈር፡በአድማስ(በመሠረት)፡ ጸንቶ ፡ እንዲኖር ፡ እንደ ፡ እዚያ ፡ ዙሪያዋን፡ጸንቶ፡እየጠበቃት፡ነው፤
ወይእዜኒ፡ተንሥኡ፡ወሑሩ፡ወፃኡ፡
አሁንም፡ተነሥታችሁ፡ውጡ፤
ዘእንበለ፡ይምጻእ፡ኃይለ፡ከላውዴዎን፤
የከላውዴዎን፡ሠራዊት፡ሳይመጣ፤
ወይዕዱ፡ለሀገር፡
አገሪቱን፡ሳይከባት፡ውጡ፤

፲፤ ወነበበ፡ኤርምያስ፡እንዘ፡ይብል፡
ኤርምያስ፡እንዲህ፡ብሎ፡ተናገረ፤
አስተበቍዓከ፡እግዚእየ፡
ጌታዬ፡እማልድሃለሁ፤
አዝዞ፡ለገብርከ፡ከመ፡ይትናገር፡ቅድሜከ፡
በፊትህ ፡ እናገር ፡ ዘንድ ፡ እኔን ፡ ባሪያህን፡እዘዘኝ፤

፲፩፤ ወይቤሎ፡እግዚእ፡
እግዚአብሔር፡እንዲህ፡አለው፤

www.ethiopianorthodox.org

በል፡ኀሩይየ፡ኤርምያስ፡
ወዳጄ፡ኤርምያስ፡በል፡ተናገር፤

፲፪፤ ወነበበ፡ኤርምያስ፡ወይቤሎ፡
ኤርምያስ፡ተናገረ፡እንዲህ፡አለው፤

እግዚኦ፡ዘከተሎ፡ትእኅዝ፡
ሁሉን፡የምትገዛ፡አቤቱ፤

ትሜጡኑ ፡ ዛተ ፡ ሀገረ ፡ ኅሪተ ፡ ውስተ ፡
እዴሆሙ፡ለከለዳውያን፡
የተመረጠች ፡ ይችን ፡ ሀገር ፡ በከለዳ
ውያን፡እጅ፡አሳልፈህ፡ትሰጣታለህ?

ከመ፡ይዘኃር፡ንጉሥ፡ምስለ፡ሕዘቢሁ፡
ንጉሡ ፡ ከሠራዊቱ ፡ ጋራ ፡ ይታበይ ፡
ዘንድ፤

ወይበል ፡ ተኀየልኩ ፡ ውስተ ፡ ሀገር ፡
ዘአምላክ፡
የእግዚአብሔር፡ማደሪያ፡በምትሆን፡
በኢየሩሳሌም ፡ ተበረታታሁባት ፡
ይል፡ዘንድ፤

፲፫፤ ሐሰ፡እግዚኦ፡
አቤቱ ፡ ታጠፋት ፡ ዘንድ ፡ አገባብህ ፡
አይደለም፤

እመሰ፡ፈቀድከ፡በእዴከ፡አማስና፡
ልታጠፋትስ ፡ ከወደድህ ፡ እንደ ፡
ሰብአ፡ ሰዶም ፤ እንደ ፡ ሰብአ ፡ ትካት ፡
አንተ ፡ በሥልጣንህ ፡ አማስና ፡
አጥፋት፡አለው፤

፲፬፤ ወይቤሎ፡ለኤርምያስ፡እግዚእ፡
ጌታ፡ኤርምያስን፡እንዲህ፡አለው፤

እስመ፡ኀሩይየ፡አንተ፡
አንተ፡ወዳጄ፡ነህና፤

ተንሥኡ፡ወጻኡ፡አንተ፡ወባሮክ፡
አንተና፡ባሮክ፡ተነሥታችሁ፡ውጡ፤

እስመ ፡ ሀሎኩ ፡ አማስና ፡ በኃጢአቶሙ ፡
ለእለ፡ይነብሩ፡ውስቴታ፡
በውስጧ ፡ በሚኖሩባት ፡ ሰዎች ፡
ኃጢአት፡አጠፋት፡ዘንድ፡አለኝና፤

፲፭፤ ወኢንጉሥ፡ወኢኃይለ፡ዚአሁ፡
ንጉሥም፡ሁኖ፡ሠራዊቱም፡ሁኖ፤

ኢይክል፡በዊአ፡ውስተ፡ሀገር፡
ወደ ፡ ኢየሩሳሌም ፡ መግባት ፡ አይቻላ
ቸውም፤

ለእመ ፡ ኢቀደምኩ ፡ ወኢያርኀውኩ ፡
አናቅጺሃ፤
እኔ፡አስቀድሜ፡በሩን፡ከፍቼ፡ከአላስ
ገባሁ፤

፲፮፤ ተንሥእ፡ይእዜኒ፡ሑር፡ኀበ፡ባሮክ፡
አሁንም ፡ ተነሥተህ ፡ ወደ ፡ ባሮክ ፡
ሔደህ፡

ወዜንዎ፡ዘንተ፡ነገረ፡ኵሎ፡
ይህንን፡ሁሉ፡ነገር፡ንገረው፤

ተንሢአክሙ ፡ ሶበ ፡ ኮነ ፡ ፮ቱ ፡ ሰዓት ፡
ዘሌሊት፡
መንፈቀ፡ሌሊት፡በሆነ፡ጊዜ፤

ንዑ፡ውስተ፡ቅጽረ፡ሀገር
ወደ፡ከተማው፡በር፡ኑ፤

፲፯፤ ወአነ፡አርእየክሙ፤
እኔ፡የማደርገውን፡እገልጥላችኋለሁ፤

ወለእመ፡አነ፡ኢቀደምኩ፡አማስኖታ፤
እኔ፡አስቀድሜ፡ሀገሪቱን፡ካላጠፋሁ፤

ኢይክሉ፡በዊአታ፤
ወደ፡እርሷ፡መግባት፡አይቻላቸውም፤

፲፰፤ ወዘንተ ፡ ብሂሎ ፡ እግዚእ ፡ ሐለፈ ፡
እምኀበ፡ኤርምያስ፤
ጌታ ፡ ይህንን ፡ ተናግሮ ፡ ከኤርምያስ ፡
ተለይቶ፡ሔደ፡ተሠወረ፤

፲፱፤ ወሶቤሃ፡ሠጠጠ፡አልባሲሁ፡
ያን፡ጊዜ፡ኤርምያስ፡ልብሱን፡ቀደደ፤
አሰለበ፤



ወወደየ፡ሐመደ፡ላዕለ፡ርእሱ፡
በራሱ፡ላይ፡አመድ፡ነሰነሰ፤

ወቦአ፡ውስተ፡ቤተ፡መቅደስ፡
ወደ፡ቤተ፡መቅደስ፡ገባ፤

፳፤ ወርእዮ ፡ ባሮክ ፡ ለኤርምያስ ፡ እንዘ ፡
ምሉዕ፡መሬተ፡ዲበ፡ርእሱ፡
ባሮክ ፡ ኤርምያስን ፡ በራሱ ፡ ላይ ፡
ትቢያ፡ነሥንሶ፡ባየው፡ጊዜ፤

ወአልባሲሁ፡ስጡጥ፡
ልብሱን፡ቀዶ፡አስልቦ፡ባየው፡ጊዜ፤

ጸርሐ፡በቃል፡ዓቢይ፡እንዘ፡ይብል፡
እንዲህ ፡ ብሎ ፡ ቃሉን ፡ አሰምቶ ፡
ጮኸ፤

ኦ፡አቡየ፡ኤርምያስ፡ምንተ፡ኮንከ፡
አባቴ፡ኤርምያስ፡ምን፡ሆንክ፤

ወአየ፡ኃጢአተ፡ገብሩ፡ሕዝብ፡
ሕዝቡ፡ምን፡ኃጢአት፡ሠሩ፤

፳፩፤ እስመ ፡ ሶበ ፡ ስሕቱ ፡ ሕዝብ ፡
የኀዝን፡ኤርምያስ፡
ሕዝቡ ፡ በበደሉ ፡ ጊዜ ፡ ኤርምያስ ፡
ያዝን፡ነበርና፤

ወይወዲ፡ሐመደ፡ዲበ፡ርእሱ፡
በራሱ፡ላይ፡ትቢያ፡ነስንሶ፤

ወይጼሊ፡በእንተ፡ሕዝብ፡እስከ፡ይትሐደግ፡
ሎሙ፡አበሳሆሙ፡ለሕዝብ፡
የሕዝቡ ፡ ኃጢአታቸው ፡ እስኪሠረይ
ላቸው፡ድረስ፡ስለ፡ሕዝቡ፡ይጸልይ፡
ነበርና፤

፳፪፤ ወተስእሎ፡ባሮክ፡እንዘ፡ይብል፡
ባሮክ፡እንዲህ፡ብሎ፡ጠየቀው፤

አቡየ፡ኤርምያስ፡ምንተ፡ኮንከ፡
አባቴ፡ኤርምያስ፡ምን፡ሆንክ፡አለው፤

ወይቤሎ ፡ ኤርምያስ ፡ ዕቀብ ፡ ከመ ፡
ኢንስጥጥ፡አልባሲነ፡
ኤርምያስ፡ባሮክን፡ልብሳችንን፡እንዳ
ንቀድ ፡ እንዳናሰልብ ፡ አስተውል ፡
ጠብቅ፡አለው፤

አላ፡ንስጥጥ፡አልባቢነ፡
ልቡናችንን ፡ ከተድላ ፡ ከደስታ ፡
እንለይ ፡ እናርቅ ፡ እንጂ ፡ ወአኮ ፡
አልባሲነ ፡ አላ ፡ ንስጥጥ ፡ አልባቢነ ፡
እንዲል፤

፳፫፤ ወኢንደይ ፡ ማየ ፡ ውስተ ፡
ምዕቃላት ፡ ከመ ፡ ንብኪ ፡ ርቱዓ ፡ እስከ ፡
ንመልዖሙ፡አንብዓ፡
በሚገባ፡አልቅሰን፡እንባን፡እስክንመ
ላቸው ፡ ድረስ ፡ በውሃው ፡ ጕድጓድ ፡
ውሀውን ፡ እንመላ ፡ ዘንድ ፡ አን
ጨምር፤

እስመ ፡ እምይእዜ ፡ ኢይምህርዎሙ ለዝ ፡
ሕዝብ፡
ከዛሬ፡ጀምሮ፡እነዚህን፡ወገኖች፡አይ
ራሩላቸውምና፤

፳፬፤ ወይቤ፡ባሮክ፡አቡየ፡ኤርምያስ፡
ምንተ፡ኮንከ፡
ባሮክ፡አባቴ፡ኤርምያስ፡ምን፡ሆንህ፡
አለ፤

፳፭፤ ወይቤሎ፡ኤርምያስ፡
ኤርምያስ፡እንዲህ፡አለው፤

እስመ፡አምላክ፡ይሜጥዋ፡ለሀገር፡ውስተ፡
እዴሁ፡ለንጉሠ፡ከላውዴዎን፡
እግዚአብሔር ፡ ኢየሩሳሌምን ፡ በከላ
ውዴዎን፡ንጉሥ፡እጅ፡አሳልፎ፡ይሰ
ጣታልና፤

እስመ፡ለሕዝብ፡በእኪት፡ይጼውዎሙ፡
ሕዝቡን ፡ በክፉ ፡ መከራ ፡ የሚማር
ካቸው፡ስለሆነ፤

www.ethiopianorthodox.org

፳፮፡ ወሰሚዖ፡ዘንተ፡ኵሎ፡ባሮክ፡
ባሮክ፡ይህን፡ሁሉ፡ሰምቶ፤
ወይቤ፡አቡየ፡ኤርምያስ፡
አባቴ፡ኤርምያስ፡አለ፤
ውእቱኒ፡ሰጠጠ፡አልባሲሁ፡
እርሱም፡ልብሱን፡ቀደደ፤አሰለበ፤
ወይቤ፡ምንተ፡ለአኩ፡ለከ፡
ሥላሴ፡ለአንተ፡ምን፡ላኩ፡አለው፤

፳፯፡ ወይቤሎ ፡ ኤርምያስ ፡ ጽናሕ ፡ ምስሌየ፡እስከ፡፮ቱ፡ሰዓት፡ዘሌሊት፡
እስከ ፡ ስድስተኛው ፡ ሰዓተ ፡ ሌሊት ፡ ድረስ፡ከእኔ፡ጋራ፡ቆይ፡አለው፤
ከመ፡ታእምር፡በአማን፡ነገረ፡
ነገሩን፡በእውነት፡ታውቅ፡ዘንድ፤

፳፰፡ ወነበሩ ፡ በቤተ ፡ መቅደስ ፡ እንዘ ፡ ይበክዩ፡
እያለቀሱ ፡ በቤተ ፡ መቅደስ ፡ ደጅአፍ፡ ተቀመጡ፤
ወሶበ ፡ ኮነ ፡ ፮ቱ ፡ ሰዓት ፡ ዘሌሊት ፡ ዘይቤሎ ፡ ለኤርምያስ፡እግዚእ፡ከመ፡ይፃእ፡
ወደ ፡ ቤተ ፡ መቅደስ ፡ ይወጣ ፡ ዘንድ ፡ ጌታ ፡ ለኤርምያስ ፡ ስድስተኛው ፡ ሰዓተ፡ሌሊት፡በደረሰ፡ጊዜ፤

፳፱፡ ወወጽአ፡ምስለ፡ባሮክ፡
ከባሮክ ፡ ጋራ ፡ ወደ ፡ ቤተ ፡ መቅደስ ፡ ወጣ፤
ወበጽሑ፡ውስተ፡ቅጽር፡
ከቤተ፡መቅደስ፡ቅጽር፡ደረሱ፤
ወነበሩ፡እንዘ፡ይጼልዩ፡
እየጸለዩ፡ተቀመጡ፤
ወኮነ፡ቃለ፡ቀርን፡
ግባ ፡ ግባ ፡ የሚል ፡ የነጋሪት ፡ ድምፅ ፡ ተሰማ፤

፴፡ ወመጽኡ፡መላእክት፡እምሰማያት፡
ከሰማይ፡መላእክት፡መጡ፤
ወበእደዊሆሙ፡ይፀውሩ፡ብርሃናተ፡እሳት፡
የእሳት ፡ ብርሃን ፡ ይዘው ፡ ፂሐ ፡ ፂሐቸውን ፡ ችቦአቸውን ፡ እያበሩ ፡ መጡ፤
ወቆሙ፡ውስተ፡ቅጽር፡
በቤተ፡መቅደስ፡ቅጽር፡ቆሙ፤

## ምዕራፍ ፡ ፶፩ ፡

፩፡ ወሶቤሃ ፡ ኤርምያስ ፡ ወባሮክ ፡ በከዩ ፡ እንዘ፡ይብሉ፡
ያንጊዜ፡ኤርምያስና፡ባሮክ፡እንዲህ፡ እያሉ፡አለቀሱ፤
እስመ ፡ ይእዜ ፡ አእመርነ ፡ ከመ ፡ በአማን ፡ ተረክበ፡ትእምርተ፡ዝንቱ፡ነገር፡
የዚህ፡ነገር፡ምልክቱ፡በእውነት፡እን ደተገኘ ፡ ዛሬ ፡ አውቀናል ፤ ተረድተ ናልና፤እንድም፡ከመ፡አማን፡ቢል፡ የዚህ ፡ ነገር ፡ ምልክቱ ፡ እውነት ፡ እንደሆነ፡አውቀናል፡ተረድተናልና፤

፪፡ ወአስተብቍዖሙ ፡ ኤርምያስ ፡ ለመላ እክት፡እንዘ፡ይብል፡
ኤርምያስ ፡ መላእክትን ፡ እንዲህ ፡ ብሎ፡ማለዳቸው፤
አስተበቍዓክሙ፡ኵሎ፡ኢታኅጕሉ፡ሀገረ፡ እስከ ፡ እስዕሎ ፡ ለእግዚአብሔር ፡ አሐተ ፡ ነገረ፡
እግዚአብሔርን፡አንዲት፡ነገር፡እስከ ምለምነው ፡ ድረስ ፡ ማለት፤ ከእግዚአ ብሔር፡ጋራ፡የምነጋገረው፡እለኝና፡ ሀገሩን ፡ ሁሉ ፡ እንዳታጠፉ ፡ ቆዩኝ ፡ አላቸው፤

፫፡ ወነበቦሙ ፡ እግዚእ ፡ ለመላእክት ፡ እንዘ፡ይብል፡
[illegible]፡አላቸው፤
ኢታኅጕሉ ፡ ሀገረ ፡ እስከ ፡ እትናገር ፡ ምስለ ፡ ኤርምያስ፡ኅሩይየ፡
ከወዳጄ ፡ ከኤርምያስ ፡ ጋራ ፡ የምነጋ ገረው ፡ አለኝና ፡ ሀገሩን ፡ ሁሉ ፡ እንዳ ታጠፉ፡ቆዩ፡አላቸው፤



፬፡ ወሶቤሃ ፡ ተናገረ ፡ ኤርምያስ ፡ እንዘ ፡ ይብል፡
ያን ፡ ጊዜ ፡ ኤርምያስ ፡ እንዲህ ፡ ብሎ ፡ ተናገረ፤
አስተበቍዓከ፡እግዚእየ፡
ጌታዬ፡እማልድሃለሁ፤
አዝዝ፡ሊተ፡ከመ፡እትናገር፡ምስሌከ፡
ከአንተ ፡ ጋራ ፡ እነጋገር ፡ ዘንድ ፡ እዘዘኝ፤
ወይቤሎ ፡ ንብብ ፡ ኅሩይየ ፡ ኤርምያስ ፡ ዘትፈቅድ፡
ከወገኖቼ ፡ ከእስራኤል ፤ እንድም ፡ ከወዳጆቼ ፡ ከነቢያት ፡ ለይቼ ፡ የመረ ጥኩህ ፡ ወዳጄ ፡ ኤርምያስ ፡ የምትወ ደውን፡ነገር፡በል፡ተናገር፡አለው፤

፭፡ ወይቤሎ፡ኤርምያስ፡
ኤርምያስ፡እንዲህ፡አለው፤
ናሁ ፡ ይእዜ ፡ አእመርኩ ፡ እግዚእየ ፡ ከመ ፡ ትመጥዋ፡ለሀገር፡ውስተ፡እደ፡ጸላዕታ፡
ጌታዬ ፡ ኢየሩሳሌምን ፡ በጠላቶቿ ፡ እጅ፡አሳልፈህ፡እንድትሰጣት፡እነሆ፡ ዛሬ፡አወቅሁ፡ተረዳሁ፤
ወይትነሥኡ፡ሕዝብ፡ዘባቢሎን፡
የባቢሎን ፡ ሰዎች ፡ እጅ ፡ እንዲያደ ርጓት፡እንዲማርኳት፡አወቅሁ፤
ወምንተ፡ትፈቅድ፡እግበር፡በእንተ፡ንዋየ፡ ቅድሳተ፡ቅኔነ፡በኅቡዕ፡ዘንትቀነይ፡
በእንተ፡ቅድሳተ፡ቅኔነ፡ዘንትቀነይ፡ በኅቡዕ፡ሲል፡ነው፤በምሥጢር፡የም ናገለግልባቸው ፡ የንዋየ ፡ ቅድሳቱ ፡ የእለ፡ተቅዋመ፡ወርቅ፡የእለ፡መሶበ፡ ወርቅን ፡ ነገር ፤ እንድም ፡ በመጋረ ጃው፡የምናገለግልባቸው፡ስለ፡ንዋየ፡ ቅድሳቱ ፡ ምን ፡ አደርግ ፡ ዘንድ ፡ ትወዳለህ፤

፮፡ ወምንተ ፡ ትፈቅድ ፡ እግበር ፡ ዲቤሆሙ፡
በእነርሱ ፡ ላይ ፡ ምን ፡ አደርግ ፡ ዘንድ ትወዳለህ፡አለው፤

፯፡ ወይቤሎ፡እግዚእ፡ንሥኦሙ፡
ጌታ፡ውሰዳቸው፡አለው፤
ወመጥዋ፡ለምድር፡
ለምድር፡አደራ፡ስጣት፤
ወለቤተ፡መቅደስ፡እንዘ፡ትብል፡
ለቤተ ፡ መቅደስም ፡ እንዲህ ፡ ብለህ ፡ አደራ፡ስጣት፡አለው፤
ወአንቲኒ ፡ ምድር ፡ ስምዒ ፡ ቃለ ፡ እግዚአ ብሔር ፡ ፈጣሪኪ ፡ ዘፈጠረኪ ፡ በኃይለ ፡ ማያት፡
አንቺም ፡ ምድር ፡ ማያትን ፡ (ውሀዎችን)፡ በፈጠረበት ፡ ሥልጣኑ ፤ እንድም፡ሰማያተ፡ይላል፤መላእክትን፡ ሰማያትን ፡ በፈጠረበት ፡ ሥልጣኑ ፡ የፈጠረሽ ፡ የእግዚአብሔርን ፡ ቃል ፡ ስሚ፤
ዘኅተመኪ፡በ፲ቱ፡ማኅተም፡
በፍጹም ፡ ሥልጣኑ ፡ የፈጠረሽ ፡ ምድር፤ እንድም ፡ ከሰባት ፡ የከፈለሽ ፤ እንድም ፡ በሰባቱ ፡ ዕለታት ፡ እንድት መገቢ ፡ ያደረገሽ ፡ የእግዚአብሔርን፡ ቃል ፡ ስሚ፤ የሌላ ፡ ቤት ፡ ትርጓሜ ፡ ጌታ፡ይህንን፡ዓለም፡ከሰባት፡ከፍሎ፡ በአንዱ፡ዕፃ፡ሌዋታንን፡ውቅያኖስን፡ አኑሮበታል ፤ በሁለተኛው ፡ ዕጣ ፡

www.ethiopianorthodox.org

ብሔሞትን ፡ ከነምግቡ ፡ አኑሮበታል ፤ በአምስቱ ፡ እፃ ፡ (እጣ) ፡ ሰውን ፡ እንስ ሳትን ፡ ግሩማን ፡ አራዊትን ፡ ባሕሩን ፤ የብሱን ፡ ይዘን ፡ እኛ ፡ እንድንኖርበት ፡ አድርጓል ፤

ተመጠዊ ፡ ስነኪ ፡

ብርት ፡ የሚለቀም ፡ ከመሬት ፡ ነውና ፡ ስነኪ ፡ አለ ፤ ምድር ፡ አደራሽን ፡ ተቀበዩ ፤

ወዕቀቢ ፡ ንዋየኪ ፡ እስከ ፡ ምድአቱ ፡ ለፍቁር ፡

ወጥተዋል ፡ ቢሉ ፡ እሰከ ፡ ዘሩባቤል ፡ አልወጡም ፤ ቢሉ ፡ ፍቁር ፡ ጌታ ፡ እስከ ሚመጣበት ፡ እስከ ፡ ምጽአት ፡ ድረስ ፡ አደራሽን ፡ ጠብቂ ፤

ወነበበ ፡ ኤርምያስ ፡ ወይቤ ፤

ኤርምያስ ፡ ተናገረ ፡ እንዲህ ፡ አለ ፤

አስተበቍዓከ ፡ እግዚእየ ፡

ጌታዬ ፡ እማልድሃለሁ ፤

፰፡ አርእየኒ ፡ ዘእገብር ፡ ለአቤሜሌክ ፡ ኢትዮጵያዊ ፡ ዘውእቱ ፡ ብዙኀ ፡ አቀበሙ ፡ ለሕዝብ ፡

እስራኤልን ፡ ብዙ ፡ ጊዜ ፡ ነቅቶ ፡ ተግቶ ፡ ለጠበቃቸው ፡ የኢትዮጵያ ፡ ሰው ፡ ለሚሆን ፡ ለአቤሜሌክ ፡ የማደርግ ለትን ፡ አሳየኝ ፡ አለው ፤ ይህ ፡ አቤሜሌክ ፡ መጻሕፍተ ፡ ብሉያትን ፡ ለመማር ፡ ሒዶ ፡ የኤርምያስ ፡ ደቀ ፡ መዝሙር ፡ ሁኖ ፡ ይኖር ፡ ነበር ፤

ወለገብርከኒ ፡ ኤርምያስ ፡ ፈድፋደ ፡ እምኵሉ ፡ ሰብእ ፡ ሀገር ፤

ከሀገራችን ፡ ሰዎች ፡ ሁሉ ፡ ይልቅ ፡ ነቅቶ ፡ ተግቶ ፡ እኔን ፡ ባሪያህን ፡ ለጠበቀኝ ፤

፱፡ ወውእቱ ፡ አውጽአኒ ፡ እምውስተ ፡ ዓዘቅት ፡ ዓምዓም ፡

ከንጉሡ ፡ ተካሶ ፡ እኔን ፡ ባሪያህን ፡ ረግረግ ፡ ካለበት ፡ ከአዘቅተ ፡ ኰስህ ፡ ላወጣኝ ፡ ለሱ ፡ የማደርግለትን ፡ ግለ ጥልኝ ፤

ወኢይፈቅድ ፡ ሎቱ ፡ ይርአይ ፡ ሙስናሃ ፡ ወሐጕላ ፡ ለሀገር ፡ ከመ ፡ ኢይኅዝን ፡

እንዳያዝንብኝ ፡ የኢየሩሳሌምን ፡ ፍፁም ፡ ጥፋቷን ፡ ያይ ፡ ዘንድ ፡ አይወድምና ፤ አንድም ፡ ኢይፈቅድ ፡ ሎቱ ፡ ቢል ፡ ለኤር ምያስ ፡ ሰጥቶ ፡ ነው ፤ የኢየሩሳሌምን ፡ ጥፋት ፡ አይ ፡ ዘንድ ፡ አልወድምና ፤

፲፡ ወይቤሎ ፡ እግዚእ ፡ ለኤርምያስ ፡

ጌታ ፡ ኤርምያስን ፡ እንዲህ ፡ አለው ፤

ፈንዎ ፡ ውስተ ፡ ዐፀደ ፡ ወይን ፡ ዘአግሪጳስ ፡ በፍኖተ ፡ ገዘ ፡ ደብር ፤

በዚህ ፡ በተራራው ፡ ጐዳና ፡ የአግሪጳስ ፡ ወይን ፡ ቦታ ፡ ወደሚሆን ፡ ለድውይ ፡ የምንቀባው ፡ ዕፀ ፡ በለስ ፡ አምጣ ፡ ብለህ ፡ ቅንብቻውን ፡ ትራንትራውን ፡ አሲዘህ ፡ ስደደው ፤

ወአነ ፡ እከድኖ ፡ እስከ ፡ አገብአሙ ፡ ለሕዝብ ፡ ውስተ ፡ ሀገር ፤

እስራኤልን ፡ ወደ ፡ ሀገራቸው ፡ ወደ ፡ ኢየሩሳሌም ፡ እስከመልሳቸው ፡ ድረስ ፡ እኔ ፡ በጥበቤ ፡ እሠውረዋለሁ ፡ አለው ፤

፲፩፡ ወአንተ ፡ ኤርምያስ ፡ ሑር ፡ ምስለ ፡ ሕዝብ ፡ ውስተ ፡ ግብፅ ፡ እስከ ፡ ትበጽሕ ፡ ምድረ ፡ ባቢሎን ፤

ኤርምያስ ፡ አንተ ፡ ግን ፡ የባቢሎን ፡ ሰዎች ፡ ከሠፈሩበት ፡ ሀገር ፡ እስክት ደርስ ፡ ድረስ ፡ ከሕዝቡ ፡ ጋራ ፡ አብረ ሃቸው ፡ ወደ ፡ ግብፅ ፡ ሒድ ፤

ወንበር ፡ ትትነበይ ፡ ሎሙ ፡ እስከ ፡ አገብአሙ ፡ ውስተ ፡ ሀገሮሙ ፤

ወገኖቼ ፡ እስራኤልን ፡ ወደ ፡ ሀገራ ቸው ፡ እስክመልሳቸው ፡ ድረስ ፡ ከሊ ብሀ ፡ እያንቃህ ፡ ከአፍህ ፡ እያወጣህ ፡ ትንቢት ፡ ትናገርላቸው ፡ ዘንድ ፡ አብረ ኻቸው ፡ ኑር ፡ አለው ፡

፲፪፡ ወለባርክስ ፡ ሕድጎ ፡ ህየ ፡ ውስተ ፡ ኢየ ሩሳሌም ፡

ባሮክን ፡ ግን ፡ አዕመ ፡ አበውን ፡ ይጠብቅ ፡ ዘንድ ፡ በኢየሩሳሌም ፡ ተወው ፡ አለው ፡

ወነገሮ ፡ እግዚእ ፡ ዘንተ ፡ ኵሎ ፡ ለኤርምያስ ፡

ጌታ ፡ ይህን ፡ ሁሉ ፡ ለኤርምያስ ፡ ነገረው ፡ አንድም ፡ ይህን ፡ ሁሉ ፡ ከነገረው ፡ በኋላ ፤

ወሐለፈ ፡ እግዚእ ፡ እምኔሁ ፡ ኤርምያስ ፡ ውስተ ፡ ሰማይ ፡

ጌታ ፡ ከኤርምያስ ፡ ተለይቶ ፡ የምስ ጋናው ፡ ማደሪያ ፡ ወደምትሆን ፡ ወደ ፡ ሰማይ ፡ ወጣ ፡ ዓረገ ፡ ብትልም ፡ ለእርሱ ፡ ስለ ፡ መሰለው ፡ ነው ፤ ይህስ ፡ እንደ ምነው ፡ ቢሉ ፡ ለኤርምያስ ፡ ባሮክ ፡ አቤሜሌክ ፡ የሚባሉ ፡ ሁለት ፡ ደቀ ፡ መዛሙርት ፡ ነበሩት ፡ አሁን ፡ ደቀ ፡ መዛሙርቱ ፡ እሊህ ፡ ብቻ ፡ ናቸው ፡ ማለት ፡ አይደለም ፤ ነገር ፡ ያላቸውን ፡ ለይቶ ፡ መናገር ፡ ነው ፡ እንጂ ፡ ኤርምያስ ፡ በነቢይነት ፡ መነሣቱ ፡ ኢዮስያስ ፡ ከነገሠ ፡ ከአሥራ ፡ ሦስት ፡ ዘመን ፡ ጀምሮ ፡ ነው ፤ ያን ፡ ጊዜ ፡ ነቢይነት ፡ ተሰጥቶት ፡ አባር ፡ ቸነፈርን ፡ ዌዋዌን ፡ ሚጠትን ፡ ተናገረ ፡ እነሡም ፡ ይህን ፡ ሰምተው ፡ ኢታርእየነ ፡ ሙስናሃ ፡ ለሀገር ፡ እያሉ ፡ ይጸልዩ ፡ ነበር ፡ ኋላ ፡ ጌታ ፡ ያ ፡ የነገ ርኩህ ፡ ዌዋዌ ፡ ሳይደረግ ፡ የሚቀር ፡ አይደለም ፡ አለው ፡ ምንት ፡ እግበር ፡ በእንተ ፡ ንዋየ ፡ ቅድሳቲነ ፡ ዘንትቀነይ ፡ በኀቡዕ ፡ አለው ፡ አንተና ፡ ባሮክ ፡ ወደ ፡ ቤተ ፡ መቅደስ ፡ ቅጽር ፡ ኑ ፡ አለው ፡

፲፫፡ ኤርምያስ ፡ ወባሮክ ፡ ቦኡ ፡ ውስተ ፡ ቤተ ፡ መቅደስ ፡



ኤርምያስና ፡ ባሮክ ፡ ተያይዘው ፡ ወደቤተ ፡ መቅደስ ፡ ገቡ ፡

ወነሥኡ ፡ ንዋየ ፡ ዘቅኔሆሙ ፡ መጠውዎ ፡ ለምድር ፡ በከመ ፡ አዘዞሙ ፡ እግዚእ ፡

ጌታ ፡ የሚያገለግሉባቸው ፡ ንዋየ ፡ ቅድሳቱን ፡ እለ ፡ ተቅዋመ ፡ ወርቅን ፡ ለምድር ፡ አደራ ፡ ስጧት ፡ ብሎ ፡ እንደ ፡ አዘዛቸው ፡ የሚያገለግሉባቸው ፡ ንዋየ ፡ ቅድሳቱን ፡ ለምድር ፡ አደራ ፡ ሰጧት ፤

ወሶበ ፡ ሠረበቶ ፡ ምድር ፡

ምድርም ፡ ያን ፡ ጊዜ ፡ አደራዋን ፡ ተቀበለች ፤

፲፬፡ ወነበሩ ፡ ፪ሆሙ ፡ ወበከዩ ፡

ሁለቱም ፡ በቤተ ፡ መቅደስ ፡ ደጃፍ ፡ ተቀምጠው ፡ አለቀሱ ፤

## ጉባዔ ፡


ወበሳኒታ ፡ ጸቢሖ ፡ ፈነዎ ፡ ኤርምያስ ፡ ለአቢ ሜሌክ ፡

ኤርምያስ ፡ በማግሥቱ ፡ ሲነጋ ፡ አቤሚ ሌክን ፡ ድውይ ፡ የምንፈውስበት ፡ ዕፀ ፡ በለስን ፡ አምጣ ፡ ብሎ ፡ ላከው ፡ ዕፀ ፡ በለስን ፡ ቆርጦ ፡ ሲመለስ ፡ በጊዜ ፡ ቀትር ፡ ዋዕየ ፡ ፀሐይ ፡ ጸናበት ፡ ወርእየ ፡ ዕፀ ፡ ጽፍቅተ ፡ እንዲል ፡ ጽፍቅ ፡ (ጭፍቅ) ፡ ያለዱር ፡ አይቶ ፡ ሒዶ ፡ ገብቶ ፡ ተኛ ፤ በስድሳ ፡ ስድስት ፡ ዘመኑ ፡ ከእንቅልፉ ፡ ቢነቃ ፡ ጊዜ ፡ አገኛኘቶት ፡ ከሰዓቱ ፡ ጥቂት ፡ እልፍ ፡ ብሎ ፡ አገኘው ፡ ዘግይቼ ፡ ይሆን ? መምህሬ ፡ ኤርምያስ ፡ ይቈጣኝ ፡ ይሆን ? ብሎ ፡ ከፍቶ ፡ ቢያይ ፡ ደሚ ፡ ሲንጸ ፈጸፍ ፡ ቅጠሏ ፡ ሳይጠወልግ ፡ አገኛት ፤ አልቆየሁም ፡ ብሎ ፡ መልሶ ፡ ገጥሞ ፡ ተነሥቶ ፡ መንገድ ፡ ጀመረ ፤ ሀገሩ ፡ ዳዋ ፡ ሆኖ ፡ የማያስኪደው ፡ ሆነ ፡

ታሪክ ፡ እንዳለፈው ፡

ተፈጸመ ፡ ተረፈ ፡ ነገር ፡ ዘባሮክ ፡፡

www.ethiopianorthodox.org



የብሉያት ትርጓሜና የቅኔ አብነት የነበሩት

መጋቤ ምሥጢር ጌራ ወርቅ ጥበቡ

www.ethiopianorthodox.org

www.ethiopianorthodox.org